# የኦሮሞ ብሔር ባሕል ሥርዐተ አምልኮ እና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቁርኝት

ዋቅቤካ ኤርፓ*

## Abstract

The paper's icebreaker is about the 'where' of the populous Ethiopians (the Oromo's), which has been continuously contested among different historians. Despite the earlier beliefs that the nation's origin was 'somewhere' outside Ethiopia, and then at Mada-Walabu (Bale), recent evidence witness that it has been dwelling at the Northern part of the country and with its Cushitic civilizations before it faced forced evacuation to South by the Semitic families. The theme of this research is, however, neither to assess the origin of the people nor to locate the exact geography. Instead, it is geared to show the existing similarities between the Oromo cultural/religious practices with that of EOTC, with the ultimate intention of disclosing their possible unity 'sometime' in history as well as potential future evangelization program direction by the church. The 'purposively selected locations-based' research conducted through content analysis, key informant interviews and participatory observation approaches disclosed that there exist almost perfect resemblance between the two targets in terms of: monotheistic dogmatic content (belief in just one God); spiritual blessing ceremony of the newly born babies, types, contents and practices of many holidays/feasts and festivals (like The Sabbath, Masqal /Finding of the true cross, anniversary of the elder/due to his respect for and reputes, holidays of Saints, etc), prayers and intercessions, sacrifices and divine forgiveness, criteria, rituals and responsibilities of ordination, beliefs and practices pertaining to the deceased soul; holiness and sacred things/places, and more social values. Generally, this research concludes that majority of Oromo's cultural beliefs and practices do align with that of EOTC although the 'how' and 'when' part of the alignment (assimilation) is left unanswered (forwarded for further research). It also recommends using such alliance as potential evangelization opportunities of the church, to effectively address the 'disadvantaged' people with salvation messages, instead of inconsiderately tagging their beliefs/ practices as 'animism', 'paganism' or 'idolatry'.

* ዋቅቤካ ኤርፓ በማኅበራዊ ሳይንስ የከተማ ልማት ባለሞያ

## ፩ መግቢያ :- የኦሮሞ ብሔረሰብ ዳራ በአጭሩ

ምንም እንኳን ስለ ኦሮሞ ብሔር ታሪክ በተለያዩ የታሪክ ምሁራን መካከል የተለያዩ መላምቶች ቢደመጡም የካም ዘሮች፣ ከሴም ወገኖች ቀድመው በኢትዮጵያ እንደነበሩ ብዙዎቹ ድርሳኖች ይስማማሉ፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት ‹‹በ16ኛው ክ.ዘ. በደቡብ ምሥራቅ የአገራችን ክፍል (የአሁኑ ባሌ፣ መዳ ወላቡ) በኩል ወደ ኢትዮጵያ ገባ››[1] ከሚሉት መላምቶች ይልቅ ብሔረሰቡ ከ16ኛው ክ.ዘ. በፊትም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተጠቅሷልና ይህ ጊዜ ‹ወደ መሓል ኢትዮጵያ የተጠጋበት› እንጂ ‹የተከሰተበት› አይደለም››[2] የሚለውን አሳብ እንደ መነሻ ተቀብሏል፡፡ ምክንያቱም በደቡብ ምሥራቅ ከመስፈሩ በፊትበኩሽ ነገድነቱ በሰሜን እንደነበር፣ ቀስ በቀስም ወደ ደቡብ እንደተስፋፋ የሚያትቱ መረጃዎች አሉና፡፡[3] ለዚህም ይመስላል አንዳንዶች ማኅበረሰቡ በ16ኛው ክ.ዘ. ከደቡብ ምሥራቅ በኩል ወደ መሓል አገር ያደረገው እንቅስቃሴ ‹‹አዲስ መከሰቱ›› ሳይሆን የተነጠቀ አገሩን ለማስመለስ የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ ያደረገበት ጦርነት (war of resistance) እንደሆነ የሚያስረግጡት[4]፡፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያም ኦሮሞች የካም ዘሮች መሆናቸውን ጽፈው ‹‹ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመን ነው›› የሚሉትን ድርሳናት አጥብቀው በመቃወም፣ የሴም ዘር የሆኑት ነገደ ዮቅጣን (አግዓዝያን) ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት እንኳ የካም (ኩሽ) ዘር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደነበር ያረጋግጣል፡፡[5]

ማኅበረሰቡ በወቅቱ የአርብቶ አደርነት ሕይወት የነበረው ሕዝብ ስለነበር ቀስ በቀስ ወደ መሓል አገር እየተጠጋ መጣ፡፡ እየዋለ ሲያድር ‹‹ከእርሱ የተለየ›› ሕዝብ ፤(በባሕልና በሃይማኖት) ስለገጠመው፣ እነዚያም እንደዚሁ የማያውቁትን ዓይነት ኑሮ የሚኖር ሕዝብ ስለሆነባቸው፤ ከሌሎችም አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ተደማምረው እርስ በርስ ለመዋጋት በቅተዋል፡፡ ዛሬም ድረስ በመጠኑ የሚስተዋሉ የመጋጨት ስሜቶች መነሻ ይኸው በታሪክ አጋጣሚ ታይቶ የነበረው ክስተት ይመስላል፡፡

ይህ ብሔረሰብ ከአገራችን ሕዝብ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያናችን ልትሠራ የሚገባትን ያህል ተንቀሳቅሳ በወንጌል አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ያልሸፈነች በመሆኑ፣ የአረማውያንና መናፍቃን ሰለባ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ከክልሉ ስፋት፣ ከሕዝቡም ብዛትና ስብጥር የተነሣ፤ ታሪኩንም ሆነ ባሕሉን አንድ ላይ አጠቃልሎ መዳሰስ ከባድ ነው፡፡ ለዚህም አንዱ ዐብይ ምክንያት ኦሮሞ በውስጡ ጐሣዎችና ማኅበራዊ ገጽታዎች ያሉት መሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጥናት ከብሔረሰቡ መሠረታዊ አንድነት (ጥንተ ታሪክ) አንጻር ‹‹የጋራ መገለጫ›› የሚሆኑ ጥቅል ጉዳዮች ላይ በማተኮር ከክርስትናው ይዘቶች ጋር አነጻጽሮ ለማቅረብ ይሞክራል፡፡

---

[1] በኃሮ ቢያንሣ (ተርጓሚ)፤ ‹‹*ኦሮሚያ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ*›› (አዲስ አበባ ፤ 1985 ዓ.ም፡)፤ ገጽ.13፡፡

[2] ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር)፤ ‹‹*የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፡- ኦሮሞችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ*›› (አዲስ አበባ፤1997 ዓ.ም)"ገጽ.26፡፡

[3] Biirroo Aadaa fi Tuurizimii Oromiyaa (BATO); *Seenaa Oromoo Hanga Jaarraa 16[fa]*; Gulaallii 2fa (Seeccii Duraa); Finfinnee; Waxabajjii 1998; fuula 20.

[4] ታሊላ ቡልቡላ እና ማርሳን ቦባሣ፤ «*DUDHAA*»፡ የ2001 ዓ.ም. የኢሬቻ በዓል ልዩ እትም መጽሔት በኦሮምኛ እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ፣ (2008) ገፅ 17.

[5] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ "*የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐጼ ልብነ ድንግል እስከ ዐጼ ቴዎድሮስ*" ፤ 4ኛ እትም፤ አዲስ አበባ፤1961 ዓ.ም፤ገጽ.1፣17፣94፡፡

ምንም እንኳን ብሔረሰቡበታሪክ ሂደት ውስጥ በብዙ ሥርዐተ አምልኮዎች ውስጥ ከማለፉ የተነሣ እምነቱ በቀላሉ ‹‹ይህን ይመስላል›› ለማለት ባያስደፍርም ለግንዛቤ ያህል ከጥንቱ ጀምሮ የአሁኑን ገጽታ በአጭሩ መዳሰሱ የተሻለ አማራጭ ይሆናል፡፡ ከዚያም በመቀጠል በተለይ የጥንቱ ባሕልና ሥርዐተ አምልኮ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ተዛምዶ ለማሳየት መሞከር የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ነው፡፡

## ፪ ስለ ጥናቱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ

በዓለም ውስጥ ላሉ ሕዝቦች ሁሉ ልትደርስ የሚገባት ‹‹ኩላዊት›› ቤተ ክርስቲያን ለሁሉ በሚገባው ትደርስ ዘንድ ‹‹ሁሉን ማወቅ›› ይገባታል፡፡ ይህ ሁሉን የማወቅ ጥረት ደግሞ ቀላል ስላልሆነ በሰፊ ጥናትና ምርምር እንዲሁም በዘመኑ ቴክኖሎጂ የታገዘ አካሔድ ያስፈልገዋል፡፡ በሌላ መልኩ ‹‹ሁሉን ማወቅ›› ሲባል፤ የእያንዳንዱን ‹‹ማንነት›› በአንድነት ጠቅልሎ ለማጥናትም ሆነ ለመናገር መሞከር እንዳልሆነ ግልጽ ነው፤ አንዱ ማንነት የስብጥር ‹‹ማንነቶች›› ውጤት ነውና፡፡ የሌላውን ዓለም ትተን ወደ አገራችን እውነታ ስንመጣ እንኳ በብሔረሰብ ስብጥሯ ‹‹ትንሿ ዓለም›› ሆና እናገኛታለን፡፡ ስለዚህም ‹‹አንድ አገር›› መሆኗ እንደተጠበቀ ሆኖ በውስጧ ያሉትን ‹‹የዓለም ሕዝቦች›› (የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሥርዐቶች ያሏቸውን ሕዝቦች) ‹‹እንደ አንድ›› ጨፍልቆ ለመረዳት መሞከር ‹‹ላለመረዳት›› ከሚደረገው ጥረት ቢቆጠር እንጂ እውን የሚሆን አይደለም፡፡ በተለይ የእያንዳንዱን ግለሰብ ልብ በወንጌል ቃል ማንኳኳት የሚጠበቅባት ቤተ ክርስቲያን ይህ የጥቅል አካሔድ ቢጎዳት እንጂ የሚጠቅማት አይሆንም፡፡

በአገራችን ከሚገኙት 80 በላይ ብሔረሰቦች መካከል በቁጥርም ሆነ በአሰፋፈር ሥርጭት ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው የኦሮሞ ብሔረሰብ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ልክ እንደ ቁጥሩ ብዛትና እንደ አሰፋፈሩ ስፋት ሁሉ የበርካታ ባሕሎችና ሥርዐቶች ስብጥርም ነው፡፡ በዚያው አንጻር ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅባትን ያህል በወንጌል ያልደረሰችበት ቢኖር ይኸው ብሔረሰብ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የቤተ ክርሰቲያኒቱ አቅምና ጥረት ማነስ ብቻ አይደለም፤ ባላት አቅምና ጥረት ‹‹ግብ የሚመታ›› አካሔድ አለመኖር ጭምር እንጂ፡፡ አገልግሎቷ ግቡን እንዲመታ ደግሞ የምታገለግለውን ሕዝብ ‹‹ማንነት›› (ታሪኩን፣ ቋንቋውን፣ ባሕሉን) ጠንቅቃ መረዳት ይጠበቅባታል፡፡ ይህ ሁኔታ ‹‹ራሱን ለበላው እግሩን እንደማከክ›› ይሆንባታል፡፡ ይህን በበቂ ሁኔታ ባለማድረጓ እስካሁን እንኳን በርካታ ልጆቿን ከጉያዋ ተነጥቃለች፡፡ ያሉትም ቢሆኑ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ይቀጥላሉ ብሎ ለመናገር ያስቸግራል፡፡ እናም ‹‹የተንገዳገዱ እስኪወድቁ ድረስ›› ዝም ማለት ተገቢ ስላልሆነ ይህ ጥናት የጥረቷ አንድ ነቁጥ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን በተለይ በኦሮሚያ ክልልም ለሚኖራት ሐዋርያዊ ተልእኮዋ ስኬት አስቀድማ የማኅበረሰቡን ባሕልና ታሪካዊ ዳራ ማጥናት (ማወቅ) ይኖርባታል፡፡ ይህ ሲባል ደግሞ የጥንቱን ‹‹በመኮነን›› አዲስ ትምህርት ለማስጨበጥ እንዲያመቻት በሚል አቅጣጫ ብቻ መታየት የለበትም፡፡ ይህ በአብዛኛው አላስፈላጊና እጅግ ድካምን የሚጠይቅ፣ ውጤታማነቱም አጠያያቂ ነው፡፡ ተመራጩ አካሔድ ‹‹ሌላ መሠረት ከመመሥረት›› ይልቅ ነባር የማኅበረሰቡን ድርጊቶችን ጠንቅቆ አውቆ በዚያው ላይ ማነጽ ነው፡፡ ይህን ደግሞ ለማድረግ እንደ ኦሮሞ ብሔር ከክርስትናው (በተለይ ከኦሪቱ) አካሔድ ጋር የተመሳሰለ ‹‹መሠረት›› ያለው ያለ አይመስልም፡፡ የከዚህ በፊቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ አካሔድ ‹‹ክፍተት›› የማኅበረሰቡን ባሕላዊ ድርጊቶችና ሥርዐቶች ጠንቅቆ አለማወቁ ላይ ብቻ አልነበረም፡፡ የታወቁትንም ቢሆን ‹‹ባዕድ አምልኮ›› የሚል መለያ ለጥፎ በመኮነን ማስተማሩ ታሪክን ከማዛባቱም በላይ የተጠበቀውንም ያህል ለውጥ እንዳላመጣ ለመረዳት ከእውነታ ያለፈ ሌላ ምስክር አያሻም፡፡

በእርግጥም ቤተ ክርስቲያኒቱ ‹‹እውነቱን እውነት፣ ሐሰቱን ሐሰት›› የማለት አካሄዷ የነበረና የሚኖር ነው፡፡ ይህ ጥናት ለመጠቆም የሚፈልገው ግን ‹‹ሐሰት›› ብለን በፈረጅናቸው ውስጥ ‹‹እውነት›› ይኖር እንሆነ ማሰሱ ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ሌሎች እንደ ‹‹እውነት›› የተቀበሉትን ፈጥኖ በጭፍኑ ‹‹ሐሰት›› ከማለት ይልቅ የእነዚያንም መነሻ መመርመሩ የበለጠ አሳማኝና ምክንያታዊ አካሔድ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት የብሔረሰቡን ነባር ‹‹እሴቶች›› ከመዳሰስ፣ ከክርስትናው አስተምህሮ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ከመጠቆም፣ አማራጭ የስብከተ ወንጌል አቅጣጫንም ከማመላከት አንጻር ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

## ፪.፩ የጥናቱ ዓላማዎች

**ጥቅል ዓላማ** ፡- የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዐተ አምልኮ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የኦሮሞ ብሔረሰብ ድርጊቶችን በመለየት ቤተ ክርስቲያኒቱ በክልሉ ልትከተል የሚገባትን የሐዋርያዊ ተልእኮ አማራጭ አቅጣጫ መጠቆም ነው፡፡

### ዝርዝር ዓላማዎች

- ባሕላዊም ሆነ ሃይማኖታዊ መልክ ካላቸው የኦሮሞ ብሔረሰብ ድርጊቶች መካከል በተለይ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮ ጋር የሚመሳሰሉትን መለየት፣
- የእነዚህ ባሕሎችና ሥርዐተ አምልኮዎች መመሳሰል በምን መልኩ እንደሆነ ከታሪካዊና መጽሐፋዊ ማስረጃዎች አንጻር መተንተን፣
- የእነዚህን ድርጊቶች የት መጣ በተመለከተ መጠነኛ የታሪክ ዳሰሳ ማካሔድ፣
- እነዚህን እውነታዎች መረዳት ወደፊት ቤተ ክርስቲያን በክልሉ ለምታደርገው የሐዋርያዊ ተልእኮ ጥረት የሚኖረውን አስተዋጽኦ መጠቆም፣

## ፪.፫ የጥናቱ ወሰን

ገና ከጅምሩ ለዚህ ጥናት ‹‹ፈተና›› ይሆናል ተብለው ከታሰቡት ሁኔታዎች አንዱ በየትኛው የብሔረሰቡ ክፍል (የአገሪቱ አቅጣጫ) ላይ ማተኮር እንደሚገባ መወሰኑ ላይ ነበር፡፡ ምክንያቱም በ‹‹አንዱ›› የኦሮሞ ብሔረሰብ ውስጥ በርካታ ‹‹ኦሮሞዎች›› ስላሉና ሁሉንም በጥናቱ ውስጥ ማካተት ስለማይቻል ነው፡፡ ከዚህ እውነታ በመነሣት ይህ ጥናት ብሔረሰቡ የ16ኛው መ/ክ/ዘ አሰፋፈር አቅጣጫ ተብሎ በሚታመነው ደቡብ ምሥራቅ እና የዚህ ጥናት መነሻ የሆኑ ድርጊቶች በስፋት እንደሚስተዋሉ በሚጠረጠርበት ምዕራብ ኦሮምያ (ምሥ/ወለጋ) ላይ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ በአንጻሩ አንዳንድ የክልሉ ቦታዎች ከተለያዩ ተጽእኖዎች የተነሣ ከጥንቱ የኦሮሞ ባሕል እንደራቁ ስለሚታመን፤ ይህ ጥናት ብዙም አያተኩርባቸውም (ለምሳሌ፡- በአሁኑ ጊዜ ሐረርጌ ዐረባዊ ቅየጣ፣ ምዕራብ ወለጋ የሚስዮኖች ተጽእኖ፣ ማእከላዊ ሸዋ የከተሜነት ስሜት፣ የወሎ ኦሮሞ ደግሞ በአጎራባች ማኅበረሰቦች ባሕል የመዋጥ አዝማሚያ ይታይባቸዋል)፡፡

ምንም እንኳን ብሔረሰቡ የበርካታ ታሪካዊ፣ ባሕላዊ፣ እና ሥርዐተ እምነታዊ ድርጊቶች ባለቤት ቢሆንም ይህ ጥናት ግን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዙት ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ጥናቱ በተለይ በቤተ ክርስቲያኒቱና ብሔረሰቡ ባሕላዊ / አምልኮአዊ/ ሥርዐቶች መካከል ያለውን የአፈጻጸም መመሳሰል ከማመልከት ያለፈ በትክክል ‹‹አንድ ናቸው››፣ ኦሪታዊ መገለጫ ያላቸውንም በእርግጠኝነት ‹‹ከዕብራውያን የተወሰዱ ናቸው›› ብሎ የመደምደም አቅም አይኖረውም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ እነዚህ ድርጊቶች ምንጭና ተዛምዶ የተጻፈ ማስረጃ አልያም ተጨባጭ መረጃ እስካልተገኘ ድረስ፤ ይህ ጥናት ‹‹በግድ›› የማስተሳሰር ዓላማ የለውም፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ ለወደፊቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሐዋርያዊ ተልእኮ አማራጭ አቅጣጫ ጥቆማ ከመስጠት በስተቀር እነዚህንም ሆነ ሌሎች የማኅበረሰቡን ድርጊቶች ለማሞካሸትም ሆነ ለመንቀፍ ያለመ አለመሆኑ አስቀድሞ ሊታወቅ ይገባል፡፡

### ፪.፫ የጥናቱ  አካሔድና ዘገባ

አስቀድሞ እንደተገለጸው ሁሉንም የብሔሩ ክፍሎች ማካተት ስለማይቻል በዓላማ የተመረጡ ጥቂት የብሔረሰቡ ሥፍራዎች (ወሊጋ፣ ባሌ፣ ጉጂ እና ቦረና) የዚህ ጥናት ትኩረት ናቸው፡፡ በዋናነት መመረጣቸውም ባሌ (የጥንተ ኦሮሞ ታሪካዊ ቦታ)፣ ጉጂ እና ቦረና (የጥንቱ ባሕልና ሥርዐት በአንጻራዊነት ተጠብቆ ያለበት) እና ምሥራቅ ወሊጋ (የዚህ ጥናት ነጥቦች በብዛት የሚስተዋሉበት) ስለሆኑ ነው፡፡ በሌላ መልኩም ሲታዩ እነዚህ ቦታዎች ከሌሎች ማኅበረሰቦች ባሕል ጋር የመደባለቃቸው ሁኔታ በአንጻራዊነት አነስተኛ ስለሆነ ፤ ነባር የብሔረሰቡ ድርጊቶች ‹‹ተጠብቀው›› የቆዩባቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ አከባቢዎች በዋናነት ይጠቀሱ እንጂ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር የሚገናኙ ሁኔታዎች የሚንጸባረቁባቸው ሌሎች ክፍሎችም በመጠነኛ አሰሳ ተካትተዋል፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት ገለጻዊ መረጃዎችን የተጠቀመ ሲሆን ፣ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘባቸው ዐውዶች አኀዛዊ መረጃዎችም ተካትተዋል፡፡ እነዚህንም መረጃዎች ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ፣ የመስክ ምልከታና የመዛግብት ዳሰሳ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም ከጥናቱ ዓላማ እና ከመረጃዎቹ ሁኔታ አንጻር በማብራሪያ መልክ፣ በንጽጽር፣ በሰንጠረዥ፣ ወዘተ. ተደግፈው ተተንትነዋል፡፡

## ፫. ኦሮሞ ከሃይማኖታዊ ገጽታው አንጻር

### ፫.፩ Waaqa Tokkicha (‹‹ዋቃ ቶኪቻ››)

ኦሮሞ ከጥንቱ በእግዚአብሔር ሕልውና ያምን የነበረ ብሔረሰብ ነው፡፡ የኦሮሞዎች ‹‹የሚያምኑትም በቋንቋቸው ‹ቶኪቻ ረቢ፣ ዋቃ ኬኛ› (አንዱ እግዚአብሔር[6]፣ አምላካችን) በሚሉት ነው፡፡ ሲጸልዩም ፊታቸውን  ወደ ምሥራቅ የማዞር ልማድ አላቸው ፣ ፈጣሪያቸው በሰማይ መኖሩንም ስለሚያምኑ ወደ ሰማይም አንጋጥጠው ነው›› እንዲል[7]፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸውም ከአለቃ ታዬ መጽሐፍ ያገኙትን በመጥቀስ ኦሮሞዎች በሐዋርያ ማጣት ምክንያት ወደ አረማዊነት አዘነበሉ እንጂ አንድ ‹‹ዋቃ ጉራቻ›› (በጥሬ ትርጉሙ ‹‹ጥቁር እግዚአብሔር››) እንዳለ የሚያምኑ፣ በተቸገሩና በተጨነቁም ጊዜ ወደ ሰማይ አይተው እንደሚለማመኑት ጽፈዋል፡፡[8] ይህም የሚያሳየን እግዚአብሔር ‹‹ጥቁር›› መሆኑን አይተው  ‹‹ይህን ይመስላል›› ማለታቸውን ሳይሆን፤ ወደ ላይ አንጋጥጠው ጥቁሩን ሰማይ ስለሚመለከቱ ‹‹በሰማይ ውስጥ›› ለመሆኑ የሚመሰክሩበት አባባላቸው ነው፡፡ በሌላ መልኩ ብሔረሰቡ ዋቃን ‹‹ጥቁር›› ሲል የእግዚአብሔርን ባሕርይየት (ትዕግሥት፣ ሞገስ ፣ ሕቡዕነት ፣ ወዘተ) ለመግለጥ እንደሆነ የጻፉ አሉ፡፡[9] ይኸ የብሔረሰቡ ጥንታዊና መሠረታዊ እምነት ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ተገናዝቦ መጠቆም የዚህ ጥናት ትኩረት ስለሆነ በቀጣይ ክፍሎች በስፋት የሚዳሰስ ይሆናል፡፡

---

6 አንዳንዶች የጥንቱ የብሔረሰቡን ‹‹አንድ እግዚአብሔር›› እምነት በማሳበብ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ‹‹አማልክትን ታበዛለች›› በሚል የኀሪጥ ያዩአታል፡፡ ይህ ፍንጭ ደግሞ ቅዱሳንን ለመቃወም ሲሉ ‹‹የእግዚአብሔርን አምልኮ ይጋራሉ›› ብለው ሃይማኖቲቱን ከሚነቅፉት ፕሮቴስታንቶች እና ‹‹እግዚአብሔር አንድ ገጽ፤ አይወልድም፣ አይዋለድም›› ከሚሉት አረማውያንን ጋር አወዳጃቸው፤ ስለዚህም ረመጡ እንዳይጠፋ ተደርጎ በአዲሱ ትውልድ ውስጥ ተቀጣጠለ፡፡ እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን ምእመናኗ ‹‹ባዕድ አምልኮ›› እንዳይከተሉ ስታስተምር ጠላቶቿ ግን እውነትን በፖለቲካ ቀላቅለው ‹‹የማኅበረሰቡን ባሕል ለመንቀፍ ስትል ነው›› ብለው ብዙዎችን አስደነበሩ፡፡

7 ጀቤሣ እጆታ (ባላምበራስ)፤ ‹‹የኦሮሞ ብሔር ባሕልና አጭር ታሪክ››፤ (አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት) ገጽ.93፡፡

8 ጌታቸው፣ ገጽ 177::

9 ታሊላ እና ማርሳን፣ ገጽ 35::

### ፫.፪ Qaalluu (‹‹ቃሉ››)

እንደ ብሔሩ እምነት የአንዱን ‹‹ዋቃ›› መለኮታዊ ኃይል በብዙ መልኩ ሊገልጹ የሚችሉ ‹‹አያና›› የተባሉ አያሌ ቅዱሳት-መሰል ኃይላት[10] ያሉ ሲሆን በአያና እና ኦሮሞ መካከል ደግሞ የሰመረ ግንኙነት ይኖር ዘንድ እንደ ድልድይ ሆነው የሚያገናኙት ‹‹ቃሉ›› ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነዚህ በብሔረሰቡ ጥንተ ታሪክ ውስጥ ‹‹ትንቢት የመናገር›› ወይም የንግርት ‹‹ጸጋ›› የነበራቸውና በ‹‹ዋቃ›› እና በሕዝቡ መካከል ሆነው መረጃ የሚሰጡ ተብለው ይታመኑ ነበር፡፡ በተለይ ክፉና ጥሩ ቀናትን በመለየት፣ ለሕዝቡ እንቅስቃሴ መሪ የሆነውን ‹‹ባሕረ ሐሳብ›› በመቀመር እና እነርሱ ‹‹ከእግዚአብሔር የተላከ›› የሚሉትን መልእክት በማቀበል ሕዝቡን በማገልገል ይታወቁ ነበር፡፡[11] ምንም እንኳን «ቃሉ» በሕዝቡ ባሕላዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ አመራር ውስጥ ወሳኝ ሚና ሲጫወት የነበረ ታሪካዊ ተቋም ቢሆንም አሁን አሁን ግን በአብዛኛዎቹ አከባቢዎች የሚሰገድለት (የሚመለክ) ሆኗል፡፡

### ፫.፫ ባዕድ አምልኮ

በእርግጥ ኦሮሞ በጥንተ ታሪኩ ከ ‹‹ዋቃ ቶክቻ›› በቀር ሌላ የማያውቅ እንደነበር የማምለኪያ ሐውልትና ተመሳሳይ ጣዖት (አምልኮ ምስል) እንዳልነበረው ይነገራል፡፡[12] ነገር ግን ከጥንት አምልኮው (ከአምልኮተ እግዚአብሔር) መውጣቱን በውል ሳያውቀውም ሊሆን ይችላል ቀስ በቀስ ያፈገፈገበትም ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው አስቀድሞ ‹‹ዋቃ ቶኪቻ›› ብሎ ያምን የነበረ ሕዝብ እንዴት ወደ ባዕድ አምልኮ እንደዞረ ሲያብራሩ ‹‹ሐዋርያ ስላጣ...ያየውንም ሁሉ ደግሞ ስለሚፈራ ዛፉንም፣ ወንዙንም፣ ተራራውንም ያመለከበት ጊዜ ነበር›› ብለዋል፡፡[13]

ኦሮሞ ከጥንት የአርብቶ አደርነት የተነሣ፤ አምላኩን የሚያመሰግነውም ሆነ ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚወያየው በኦዳ (ዛፍ) ሥር ነበር፡፡ ግን ገና በኦዳ ሥር ማምለክ ሲጀምር ‹‹ዋቃ ቶክቻ›› (አንድ እግዚአብሔርን) እንጂ ዛፉንና በውስጡ የሚያድሩትን አልነበረም፡፡[14] በተለይ ደግሞ የአሁኑ ትውልድ ሌላ አቅጣጫ የመያዝ አዝማሚያ እያሳየ የመጣው፡፡የጥንቱ ኦሮሞ በዛፍ ሥር እና በወንዝ ዳር ያመልክ እንደነበር ታሪክ አንብቦ ይሆናል እንጂ ማንን እና እንዴት ያመልክ እንደነበር ባለመጠንቀቁ ይመስላል፡፡

### ፫.፬ ክርስትና

የኦሮሞ ብሔረሰብ የክርስትናን ሃይማኖት መቼ እና እንዴት መቀበል እንደጀመረ መተንተን የዚህ ጥናት ዓላማ አይደለም፡፡ ዋናው ጉዳይ ግን ከጥንታዊው የ‹‹ዋቃ ቶኪቻ›› እምነቱ እና የዛፍ ሥር ወይም (የወንዝ ዳር) ሥርዐተ አምልኮው ቀጥሎ የደረሰለት ቀዳሚ ሃይማኖት ክርስትና (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በኋላ ግን በተለያዩ ምክንያቶች በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝቡ ወደ ሌሎች የእምነት ድርጅቶች ሊያዘነብል ችሏል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ሊዳሰስ የተሞከረውም የክርስትናው እና የብሔሩ ባሕል (ሥርዐተ አምልኮ) አፈጻጸም መመሳሰሉን ስለሆነ የሁለቱ ግንኙነት ከተጨባጭ አሻራዎች አንጻር ወደፊት የሚገለጽ ይሆናል፡፡

### ፫.፭ እስልምና

እኩሌታው የብሔረሰቡ አባላት ከእስልምናው ጎራ እንዲሰለፉ ያደረጓቸው ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡ በሐዋርያ ማጣት፣ ክርስትናን ይከተሉ የነበሩ መሪዎች ጥላቻ እና በግዴታ መስለም ናቸው፡፡

---

[10] ለምሳሌ፡- ማራማ የወላድ «አያና»፣ሁቴቴ የሴቶች «አያና»፣በራንቲቻ የበኩራን «አያና»ይባላሉ (ታሲሳ እና ማርሳን፣ገጽ.12).
[11] ጀቤሣ ፣ ገጽ 42፡፡
[12] በኃሮ፣ ገጽ 30፡፡
[13] ጌታቸው፣ ገጽ 174፡፡
[14] ጀቤሣ፣ ገጽ 100፡፡

አስቀድሞ በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ክፍል እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅባትን ያህል በቋንቋው አለማስተማሯ የመጀመርያው መንስኤ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የክርስትናውን ሃይማኖት ከሚከተሉት የአገሪቱ መሪዎች ጋር በነበራቸው ቅራኔ እንደነበር ፕሮፌሰር ጌታቸው ከአለቃ ታዬ መጽሐፍ እንዲህ ጠቅሰዋል፡- ‹‹ኦሮሞ ያማራን ወታደር ስለጠላ ክርስቲያን ከመሆን እስላም መሆንን ይመርጣል፡፡ ... ለዚህ እንጂ የእስላም ቢሆን የክርስቲያን ሃይማኖትን ክፋትና በጎነት ለይቶ ስላወቀ አይደለም፡፡››[15] በተመሳሳይ ሁኔታ በኃሮ የተባሉት ጸሐፊ ክስተቱ (ኦሮሞ ከክርስትና ይልቅ ወደ እስልምና ያዘነበለበት) ከነጻና ምክንያታዊ ምርጫነቱ ይልቅ ፖለቲካዊ ይዘቱ የጎላ እንደነበር ለማመልከት እንደሚከተለው ገልጸውታል[16]

> *ኦሮሞ ከአብሲኒያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ይልቅ የእስልምናን እምነት በስፋት ሊቀበሉት የበቁት የአብሲኒያውያን የክርስትና እምነት ከጭቆናቸውና ከጨቋኝ መንግሥታቸው ጋር መሳ ለመሳ አድርገው በመውሰዳቸውና ኦሮሞዎች እንደ አብሲኒያ ሕዝብ ሁሉ የተሟላ ስብእና ባለቤት መሆናቸውን ለማስመስከርም ሲሉ ነው፡፡*

እኚሁ ጸሐፊ የአቶ አጽሜ ጽሑፍ ያሉትን *‹‹...ኦሮሞ እስላም ሊሆን የበቃው በአማራው ቁስ ላይ ባለው ከፍተኛ ጥላቻ የተነሣ ነው››* የሚለውንና በረከት የተባሉ ጥናት አቅራቢ (1980) *‹‹...በአርሲ ክልል የሚኖሩት ኦሮሞዎች የእስልምናን እምነት በብዛት ሊቀበሉ የቻሉት ፀረ-አማራ ስሜታቸውን ለመግለጫና ከገዢ ኃይላት የተያያዙትን ማናቸውንም እሴቶች እንደማይቀበሉ ለማሳየት ሲሉ ነው››* ያሉትን በዋቤነት በመጥቀስ፤ ይህንኑ አሳባቸውን አጠናክረዋል፡፡ በዚያ ላይ እስልምናው ሃይማኖት ‹‹ራቢ ቶኪቻ›› በማለት ከእነርሱ ጋር ስለተመሳሰለላቸው ወደ እስልምናው እንዳዘነበሉ የጻፉም አሉ፡፡[18]

በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ተገድደው የሰለሙ የብሔረሰቡ አባላት እንደነበሩም በታሪክ ተጽፏል፡፡[19] በተለይም በሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍሎች የሚኖሩ የብሔረሰቡ አባላት የእስልምና ሰለባ ሆነው የሚገኙትም ከዚህ አንጻር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ኦሮሞነትንና እስልምናን ‹‹አንድ›› ለማስመሰል ለሚጥሩ ስጉታን እንዲያውም ሁለቱ ‹‹ደመኞች›› እንደነበሩ ማን በነገራቸው![20]

### ፫.፮ ፕሮቴስታንት

ይህ ደግሞ በተለይ በምዕራቡ የአገራችን ክፍል ያለው ብሔረሰቡ ክፍል በብዛት ያለበት ነው፡፡ አስቀድሞም እንደተገለጸው ብሔረሰቡ በራሱ ቋንቋ ወንጌል ባለመማሩ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመርያ ጊዜ በአፋን ኦሮሞ ተርጉመው (በአባ ገመቺስ ወይም በመካነ የሱስ ክርስትና ስሙ አናሲሞስ ነሲቡ በሚባለው ሰው አማካኝነት) ስላቀረቡለት ብቻ ‹‹ወንጌልን ተማረ››፡፡ *‹‹በገዛ ቋንቋቸው ሲናገር በሰሙ ጊዜ ይበልጥ ዝም አሉ››* ተብሎ እንደተጻፈ (ሐዋ.22፥2) ከሚነገረው ምንነት ይልቅ በቋንቋው ስለተነገረው በእምነቱ ተሳበ፡፡ በተለይ የመካነ የሱስ ‹‹ሲኖዶስ›› መቀመጫ እና የሌሎችም የፕሮቴስታንት ድርጅቶች ማእከል ለመሆን የበቃው ምዕራብ ወለጋ ከዚህ የተነሣ ይመስላል፡፡

[15] ጌታቸው፣ ገጽ 178፡፡
[16] በኃሮ ፣ገጽ 35፡፡
[17] ዝኒ ከማሁ፡፡
[18] ጀቤሣ፣ ገጽ 102፡፡
[19] ጌታቸው ፣ ገጽ 178፡፡
[20] ዝኒ ከማሁ ፣ገጽ 25፡፡

በአጠቃላይ ምንም እንኳ አብዛኞቹ የብሔረሰቡ አባላት ባሕላዊውን ሥርዐተ አምልኮ ሙሉ በሙሉ ባይለቁም [21] በ1999/2000 ዓ.ም. በተደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሠረት የብሔረሰቡ የእምነት ስብጥር ሲታይ በከተማ (12%) መካከል ባሕላዊ ፣ ኦርቶዶክስ 51.2%፣ እስልምና 29.9%፣ ፕሮቴስታንት17.5% ሲሆን፤ በገጠር (88%) ደግሞ ባሕላዊ 3.3%፣ ኦርቶዶክስ 47.5%፣ እስልምና 30.5%፣ ፕሮቴስታንት 17.7% መሆኑ ታውቋል፡፡

## ፬ የኦሮሞ ብሔረሰብ ባሕል/ሥርዐተ አምልኮ እና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተገናዝቦ

አስቀድሞ እንደተገለጸው የኦሮሞ ብሔረሰብ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ሥርዐተ እምነቶች ውስጥ ተከፋፍሎ ቢገኝም በተለይ የጥንቱን ባሕልና ሥርዐተ አምልኮ ሁኔታ ስናጠና ግን ከኦሪቱ ሥርዐቶች ጋር የሚያመሳስሉት ነገሮች እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ ይህንኑ እውነት አንድ የማኅበረሰቡን ታሪክ የጻፉ ደራሲ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል፡-

> *‹‹በሕገ ልቦና ፈጣሪውን የሚያምን እንደመሆኑ በአፈጻጸሙ ኦሪታዊ ሃይማኖትን የሚከተል ይመስላል፡፡››*[22]

ይህ ጥናትም መሰል ግምቶችን መነሻ በማድረግ መጠነኛ ዳሰሳ አድርጎ የሁለቱን ተገናዝቦ እንደሚከተለው ለመቃኘት ሞክሯል፡፡

### ፬.፩‹‹ዋቃ ቶኪቻ›› የኦሮሞ ጥንተ መሠረተ ሃይማኖት

ምንም እንኳን በጊዜ ሂደት ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ቢያመራም ኦሮሞ ከጥንቱ ‹‹ዋቃ ቶኪቻ›› ወይም ‹‹አንዱ እግዚአብሔር›› ብሎ ያምን እንደነበር አስቀድመን ተመልክተናል፡፡ ‹‹ዋቃ›› በኦሮሞ እምነት መሠረት የሁሉ ነገር ፈጣሪ፣ የሕይወት ምንጭ፣ በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፣ ሊደረስበት የማይችል፣ የፈለገውን ማድረግ የሚችልና ተቃዋሚ የሌለው፣ ንጹሕና የእውነተኛ ፍርድ ባለቤት፣ ለወንጀልና ለቅጥፈት ትዕግሥት የሌለው (ይህ ምግባር ያላቸውን የሚቀስፍ) ነው፡፡[23] ይህንን የማኅበረሰቡን መሠረተ እምነት (‹‹ዶግማ››) በተለያዩ መገለጫዎቹ ማረጋገጥ እንችላለን፡፡

ብሔረሰቡ ባሕል ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ያለው (የድርጊቶች መጀመሪያና መጨረሻ) ”eebba” (የአዛውንቶ ምርቃት) ነው፡፡ የዚህ ምርቃት መንደርደሪያ(መቅድም) እና የኅብረት ጸሎታቸው መደምደሚያ ደግሞ የመራቂዎቹ (በተለይ አባ ቦኩዎች) ‹‹ስብከት መሰል ማስገንዘቢያ›› ነው፡፡ በዚህ የብሔረሰቡ ሥነ ቃል ውስጥ ታዲያ ሃይማኖትና ሥነ ምግባር ምን ያህል ከማንነታቸው ጋር እንደተዋሐዱ ስለምንረዳበት ባላምባራስ ጀቤሣ ያሰፈሩትን እነሆ፡-[24]

| | |
|---|---|
| Rabbitti buluu toobba; | ለእግዚአብሔር መገዛት ባሕላችን ነው፤ |
| Isa sodaachuun toobba; | እርሱን መፍራት ባሕላችን ነው፤ |
| Isaaf sagaduun toobba; | ለእርሱ መስገድ ባሕላችን ነው፤ |
| Waaqa nu uumeef soorachuun toobba; | ለፈጠረን አምላክ መሰዋዕት ማቅረብ፣ |
| Ayyaana ulfeessuun toobba; | በዓሎቻችንን ማክበር ባሕላችን ነው፤ |
| Sanbata ulfeessuun toobba; | ሰንበትን ማክበር ባሕላችን ነው፤ |
| Jecha hoodduu dhaga'uun toobba; | የአባቶቻችንን ንግር መስማት ባሕላችን ነው |
| Dhaga'anii hojii irra oolchuun toobba; | ሰምቶም መፈጸም ባሕላችን ነው፤ |
| Kan wal-lole araarsuun toobba; | የተጣላን ማስታረቅ ባሕላችን ነው፤ |
| Kan dulloome ulfeessuun toobba. | ሽማግሌዎችን ማክበር ባሕላችን ነው:: |

[21] Summary and stastical report of the 2007 population and housing census: pop. by Age and Sex pp. 110-11. F.D.R.E– population census commission Dec. 2008, Addis Ababa.

[22] ጀቤሣ ፣ ገጽ 93፡፡

[23] በኃሮ፣ ገጽ 30፡፡

[24] ጀቤሣ፣ ገጽ 97-98፡፡

ሕዝቡም ይህንን የመሪዎቹን ‹‹መመሪያ›› መቀበሉን በእያንዳንዱ ስንኝ መጨረሻ *‹‹አዎ፣ በእውነት ባሕላችን ነው››* በማለት ያረጋግጣል፡፡ ይህ የኦሮሞ ‹‹ጸሎተ ሃይማኖት›› ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም! ኦሮሞ ከጥንትም በእግዚአብሔር የሚያምን ሕዝብ መሆኑን በስም አሰያየሞቹም ይገልጻል፡፡ ‹‹ዋቅቤካ›› (እግዚአብሔር ያውቃል)፣ ‹‹ዋቅ ዋያ›› (እግዚአብሔር ይሻላል)፣ ‹‹ዋቅ ቶላ›› (እግዚአብሔር ቸር ነው)፣ ‹‹ዋቅ ጅራ›› (እግዚአብሔር አለ)፣ ወዘተ፡፡

## ፬.፪ Ammachiisaa (አመቺሣ)

‹‹አመቺሣ›› በኦሮምኛ ቋንቋ ‹‹ማሳቀፍ›› ማለት ነው፡፡ ይህ ባሕል የተወለዱ ሕፃናት በ‹‹መንፈሳውያን የሃይማኖት አባቶች›› (አባ ቦኩ፣ ሉባ፣ ባለ ውቃቢ፣ ቃሉ፣ ወዘተ) ታቅፈው የሚባረኩበት ሥርዐት ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በተወለዱ በመንፈቅ ዕድሜ እንደሚከናወን ቢገመትም ትክክለኛ ቀኑን ለመወሰን አስቀድመው ሙሉ ቀን መቁጠር ወደሚችሉት አዋቂዎች ዘንድ በመሔድ ጨረቃ የምትታይበትን ቀን አስበው ‹‹ጨጊኖ›› (ጎደሎ/መጥፎ ቀን እንደማለት ነው) በማይውልበት ዕለት ስለሚወሰን አመቺሣው ሊዘገይ ይችላል፡፡[25] በእርግጥ ብሔረሰቡ አዛውንት የወንድና የሴት ሕፃን አመቺሣ በቀናት እንደሚለያዩ (የወንዱ እንደሚቀድም) ቢናገሩም ትክክለኛውን ግን ሊናገሩ አልቻሉም፡፡

የአመቺሣ ዋና ዓላማ የተወለዱ ሕፃናት በሃይማኖት አባቶች አማካይነት ከፈጣሪያቸው ጸጋና ረድኤት እንዲያገኙበት ሲሆን፤ የሕፃኑ እናት የታቀፈችውን ልጇን ለሌላ ስታስታቅፍ ‹‹ከዚህ በኋላ ለአንተ ሰጠሁህ›› በማለት ለፈጣሪ አደራ እንደማስረከብ ነው፡፡ ልጁ ካልታቀፈ አያድግም (ይቀሰፋል)፣ ቢያድግም አይፋፋም፣ እንከን አያጣውም ተብሎ ይታመናል፡፡ ምንም እንኳን እናቲቱ በወለደች በአምስተኛ ቀኗ (ሽናኒ በሚባል ሥርዐት) በተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎች ገላዋን ታጥባ ‹‹የነጻች›› ቢሆንም የአራስነቷን ጊዜ ጨርሳ ወደ ሥርዐተ አምልኮው የምትሔደው ግን በዚህ ዕለት ነው፡፡ እርሷም አስፈላጊውን ‹‹መባ›› (አሞሌ ጨው፣ አረቂ፣ ዳቦ፣ በኑግ የታሸ ቆሎ፣ ማር፣ ወዘተ) ለልጁና ለራሷ ይዛ ሔዳ "garaa jiidhaa ta'i, ilma lammiif ta'u da'i" (‹‹ማኅፀነ ርጥብ /ወላድ/ ሁኚ፣ ለወገን የሚተርፍ ወንድ ልጅ ውለጂ››) ተብላ ትመረቃለች፡፡[26]

*ሥርዐቱ* በትክክለኛው ቀን የሕፃኑ ቤተሰቦች ወደ ሥፍራው ይወስዱትና እርጥብ ሣር ተጎዝጉዞ፣ በገል እሳት አማካኝነት በሚሸቱ ዕፀዋት ጢስ በታወደው ማምለኪያ ቤት ይገኛሉ፡፡ እናት ልጇን ታቅፋ ከፊት፣ አባት ከኋላ፣ ሌሎችም እንደ የማዕረጋቸው ሁነው ከታቃፊው ፊት ይቀርቡና ሁለት አሞሌ ጨው አበርክተው፤ ልጁን ይሰጡታል፡፡ የሃይማኖት አባትም ልጁን ታቅፎ ወደ ዋቃ ቶኪቻ እንዲህ ሲል ይጸልያል፡-[27]

> *"Yaa Rabbi hundumaa uumte, dhiiga dugda abbaatii fuute, garaa haadhaa keessatti guddiste, nama afuura qabu goote, ciniinsuu fi daha gargaarte, kan ija keenyaan nu agarsiiste, amantii guddaadhaan si galateeffanna. Akkasuma mucaa kenna keetiin jara lamaan kana gidduutti argame kana kan lammii isaa gargaaru fi bulchu, kan haadha fi abbaa isaa xooru, kan gorsa jaarsaa dhaga'u, kan tobba (aadaa) qomoo isaa eegu, kan siin sodaatee si amanee sitti bulu akka nuuf gootu garaadhaan si kadhanna. Lubbuu dheeraa kenniif, haati fi abbaan isaa erga inni dhalatee nuuf tole jedhanii akka si galateeffatan milkii gaarii godhiif; kadhaa uummata kana hundumaa dhaga'i, o! jedhii jalaa qabi, deebii nagaa deebisiif"*

[25] ጀቤሣ፣ ገጽ 160፡፡ አቶ ቤኛ ያዳታ (ቃለ መጠይቅ)፤ በምሥ/ወለጋ (ሀባቦ ጉዱሩ ወረዳ) ነዋሪና የ82 ዓመት አዛውንት፤ በተለይ ብሔረሰቡ ታሪካዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው፡፡
[26] ወ/ሮ ሀንጋራሼ ቡጢ (ቃለ መጠይቅ)፤ በምሥ/ወለጋ (ሀባቦ ጉዱሩ ወረዳ) ነዋሪና የ 75 ዓመት አዛውንት፤ ስለ ብሔረሰቡ ባሕላዊና ‹‹ሃይማኖታዊ›› እሴቶች ሊጠየቁ የሚችሉ እናት፡፡
[27] ጀቤሣ፣ ገጽ 161፡፡

**ትርጉሙ፡-** *ሁሉን የፈጠርክ እግዚአብሔር ሆይ፡- ከአባት ጀርባ /አብራክ/ ደም አንሥተህ፣ በእናት ማኅፀን ቋጥረህ እስትንፋስ ያለው አድርግህ፣ መውለድና ምጥ ረድተህ /ገላግለህ/ በዐይናችን ስላሳየኸን ከፍ ባለ እምነት እናመሰግንሃለን፡፡ እንደዚሁም ይኸንን ልጅ በአንተ ስጦታ፤ ከእነዚህ ሁለቱ የተገኘውን ወገኑን የሚረዳና የሚያስተዳድር፣ እናት አባቱን የሚጦር፣ የሽማግሌዎችን ምክር የሚሰማ፣ የጎሣውን ባሕል የሚጠብቅ፣ አንተን ፈርቶ፣ አንተን አምኖ፣ በአንተ የሚያድር እንድታደርግልን ከልብ እንለምንሃለን፡፡ ረጅም ዕድሜ ስጠው፣ እናትና አባቱ እርሱ ከተወለደ ደላን ብለው እንዲያመሰግኑህ [28] ጥሩ ጊድ አድርግላቸው፤ የእነዚህን አማኞች ሕዝቦችህን ልመና እህ ብለህ ስማ፣ የምሕረት መልስም መልስላቸው ማለት ነው፡፡*

ከዚህ በኋላ ለልጁ ስም ያወጣለታል (እናትና አባቱ ካወጡለት ሌላ)፡፡ እንትፍ ብሎ እንዲያድግ መርቆት መልሶ ይሰጣቸዋል፡፡

በመሠረቱ ይህ ሥርዐት በዘሌዋ.12፡1-8 ላይ ከተቀመጠውና ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ ሥፍራ ከሚሰጠው የ 40 እና የ80 ልጅነት ጥምቀት (ክርስትና ማስነሣት) ጋር የሚመሳሰል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እዚህ ላይ የሚገርመው ነገር ቢኖር፤ አመቺሣ የግድ ከክርስትና በፊት መፈጸሙ ነው፡፡ አንድ ሕፃን አስቀድሞ ክርስትና ከተነሣ በፍጹም አይታቀፍም፤ ይህን ያደረገ ቤተሰብም ‹‹እስከ መወገዝ›› ይደርሳል፡፡ ምክንያቱ ግልጽ ቢመስልም ስለ ሁኔታው የሚጠየቁት አዛውንት ሁሉ ግን ቁርጥ ያለ መልስ አይሰጡም፤ በቃ "qooda isaati" (ሥርዐቱ ነው) በሚል ይቋጫሉ፡፡

### ፩.፫ በዓል

የኦሮሞ ሕዝብ በየወሩና በየዓመቱ የሚያከብራቸው በዓላት አሉት፡፡ ወርኀዊ በዓላትን በየደጃቸው፣ ዓመታዊዎቹን ግን በተለዩ የአንድነት አምልኮ ቦታዎች (ዋልዳ) በመሰብሰብ ያከብራሉ፡፡ብዙዎቹ በዓላት በስያሜም ሆነ በአከባበር ሥርዐታቸው ከክርስትናው ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ በዓላት የአብዛኛዎቹን ስያሜና አከባበር ለመጻፍ የሞከሩት ባላንበራስ ጀቤሣ እጄታ በእርግጥም ሊመሰገኑ ይገባቸዋል፤ ነገር ግን ያለውን ሁኔታ በአግባቡ ከገለጡ በኋላ የራሳቸውን ማብራርያ ለመስጠት ሲሞክሩ፣ የተዛባ ነገር ያለ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ፡- ‹‹ማራማ የሚሉትና ጋራንፋሳ የሚሉ በአጋጣሚ ስም እንጂ ከክርስቲያን ሃይማኖት የተወሰደ አይደለም›› ብለዋልና፡፡[29] እንደ እውነቱ ከሆነ (በኋላም እንደምንመለከተው) ያለ ጥልቅ ምርምር እነዚህን ስያሜዎች ‹‹አጋጣሚ›› የሆኑ ናቸው ብሎ መደምደም የታሪክ ስህተተኛ ያደርጋል፡፡

በዚህች መጠነኛ ዳሰሳ ሁሉንም ማካተት ባይቻልም፣ የጥቂቶቹን በዓላት ስያሜ (ምንነታቸውን)፣ ዕለተ ክብራቸውን፣ የመከበራቸውን ዓላማ፣ የአከባበር ሥርዐታቸውንና ከክርስትናው አቻቸው ጋር ያላቸውን ተዛምዶ (ተገናዝቦ) እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ ስለ በዓላቱ የተሰነዘሩ አሳቦች ምንጭ ተለይቶ ካልተጠቀሰ በቀር ከወ/ሮ ሀንጋሬሼ እና አቶ ቤኛ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ በዋና ግብዓትነት ተወስዷል፡-

**Sanbata (ሳንባታ)** :- የኦሮሞ ብሔረሰብ ‹‹ሳንባታ›› የሚላት ቀዳሚትን ነው፡፡ ይህችን ሳንባታ ከእሑድም አስበልጦ እጅግ ያከብራታል፤ ምንም ምን ሥራ አይሠራባትም፡፡[30] እንዲያውም ሰንበት በፈጣሪ ትእዛዝ የሚከበር መሆኑን የሚያመለክት አንድ አባባል አላቸው፡- "Sanbatni kan Waaqayyooti" (ሰንበት የእግዚአብሔር ነው) የሚል፡፡

---

[28] ኦሮሞዎች ለቤተሰቦቻቸው የማይታዘዙ ልጆችን ‹‹ያወግዛሉ›› ብቻም ሳይሆን ‹‹እንዳልተወለደ›› ወይም ‹‹እንደ ሞተ›› ይቆጥሩታል። ኦሪትም እንዲህ ዓይነት ልጆች ‹‹በድንጋይ ተወግረው ይገደሉ›› ትላለች (ዘዳ.21፡18-21)። ‹‹አባቱን ወይም እናቱን የሚያቃልል ርጉም ይሁን›› ብላም ትራገማለች (ዘዳ.27፡16)።

[29] ጀቤሣ፣ ገጽ 104፡፡

[30] ዝኒ ከማሁ፣ 111-112።

በዚህች ዕለት እግዚአብሔር የለመኑትን ይሰጣል፣ የተመኙትን ያደርሳል፣ ቀኒቱን በማክበርና በመዘከርም ኃጢአት ይሠረያል ብለው ያምናሉ፡፡[31] የሰንበትን ቀን የሚሽር ቢኖር "balaa diingataatu bu'a" (ድንገተኛ መቅሰፍት ይወርዳል) ተብሎ ይታመናል፡፡

እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ Korma Sanbataa (የሰንበት ኮርማ) የሚባል አለ፡፡ ይህ ኮርማ የማያርስ፣ የማይታረድ፣ ለመንጋው ግርማ ሞገስ ሆኖ ብቻ የሚደልብ (የሚቀመጥ) ነው፡፡ ይህም ብሔረሰቡ ለሰንበት ምን ያህል ክብር እንዳለው የሚጠቁመን ሌላኛው ነጥብ ነው፡፡

ስለዚህም *Dhaabbata Sanbata (ዝክረ ሰንበት)* ይደረጋል፡፡ አስቀድሞ እንደተገለጸው ሰንበትን መዘከር ለኃጢአት ሥርየት ይጠቅማልና በዓመት አንድ ቀን ጠላ ተጠምቆ፣ ከብት ታርዶ፣ ዳቦ ተደፍቶ፣ ቡናና ቆሎ ተዘጋጅቶ የአካባቢው ሰው በተገኘበት ይከበራል፡፡ ዘካሪው በአንድ እጅ እንስሳውን/ኀብስቱን፣ በሌላኛው እጁ "gulantaa Sanbataa" (የሰንበት መደብ) አጠገብ የቆመውን የሰንበት እንስራ/ጠላውን ጨብጦ ሦስት ጊዜ መላልሶ "kuni dhaabbata Sanbataati…Sanbataaf dhaapheera" (ይህ ለሰንበት የተዘከረ ነው፣ ለሰንበት ቆሜአለሁ) ሲል ታዳሚዎቹ "Gooftaan Sanbataa fooni fi lubbuun siif haa dhaabatu" (የሰንበት ጌታ በነፍስ በሥጋ ይቁምልህ) ይሉታል፡፡ በተመሳሳይ በቅዱስ መጽሐፍ ስለ ሰንበት ክብር የሚያወሱ አምላካዊ ትእዛዛት በርካታ ናቸው (ዘፀ.20፡8፤ ዘሌዋ.23፡3፤ ኢሳ.56፡6-7)፡፡

**Masqala (መስቃላ):-** ይህ የ‹‹መስቀል›› ክብረ በዓል ሲሆን ከደመራ (ችቦ) የማቀጣጠሉ ሥርዐት ጋር ተያያዥነት አለውና ‹‹gubaa›› (በቁሙ ‹‹ማቀጣጠል››) ተብሎም ይጠራል፡፡ በዓሉም በተጨባጭ በአገራችን እንደሚታየው ብሔሩ የበዓላት ቁንጮ ነው፡፡ ምንም እንኳን በበዓሉ ላይ ባሕላዊ አምልኮዎ የሚፈጸሙበት ቢሆንም የሥርዐቱ ይዘት ግን ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን አንድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንደተለመደው ሁሉ የኦሮሞ አዛውንት ለምን ስያሜው ማስቃላ ተባለ? ለምንስ ይከበራል (ዓላማው)? ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች በመረጃ የተደገፈ አመክንዮ ማቅረብ ይሳናቸዋል፤ ብቻ ከክረምት ጨለማ ወደ ፀሐይ ብርሃን የወጣንበት ስለሆነ ከጥንት አባቶቻችን የመጣ በዓል ነው ይላሉ፡፡

በዚህ ሥርዐት ውስጥ የሚገርመው ጉዳይ ሊጥ በእርጥብ ቅጠል ጠቅልለው፤ በተቀጣጠለው ችቦ ውስጥ ያስገቡና ሲበስል ርሙጠውን ቆራርሰው ለከብቶች ያበላሉ፤ እንደ እነርሱ እምነት ይህ «የከብቶችን ሆድ ቁርጠት ይከላከላል»፡፡ በተጨማሪም "hadaa" የሚሉት አደይ አበባ ተነቅሎ ይመጣና ሥሩ በፍሙ ከሞቀ በኋላ ለሁሉም ይታደላል፡፡ ሁሉም በጥርሱ እያኘከ ሰውነቱን ያብስበታል፤ ይህ ደግሞ «እባብ እንዳይነድፍ ይከላከላል» ባይ ናቸው፡፡[32] የችቦውን አመድም በግንባራቸው የሚቀቡ በርካቶች እንዳሉ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ያውቃል፡፡

በዚህ ሁኔታ የኦሮሞ ‹‹ማስቃላ›› ሌሎች እንደሚሉት ከመስቀል ጋር የተመሳሰለው በአጋጣሚ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ሌላው ቢቀር በማስቃላ አመድ የተተኮሰ ተክል በማኘክ ሰውነቱን የደባበሰ ሰው ‹‹እባብ አይነድፈውም›› የሚል እምነት ያለው ብሔሩ ‹‹ሰይጣን በመስቀሉ ይሸነፋል›› ብሎ *ከሚያምነው፣ ‹‹…በመስቀሉ ጥልን ገድሎ…ሰላምን ሰጠን…›› (ኤፌ.2÷16)፤ ‹‹ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያቢሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ…›› (ራእ.12÷9)* ከሚለው በመጽሐፍ ቅድሳዊ ጭብጥ በአገላለጽ ካልሆነ በቀር በይዘት አይራራቅም፡፡

[31] ዝኒ ከማሁ፡፡
[32] ጀቤሣ፣ ገጽ 105፤ አቶ ቤኛ (ቃለ መጠይቅ)፡፡

**Boorenticha (ቦረንቲቻ) (ክብረ ‹‹ብኩርና››)** :- *የቃሉ ሥርወ መገኛ የኦሮሞ ቀዳሚያን ‹‹ግንዶች›› የሚባሉት ሁለቱ ወንድማማቾች*[33] *ናቸው:- ቦረና (ታላቅ) እና ባሬንቱ (ታናሽ)፡፡ በኦሮሞ ዘንድ ደግሞ ብኩርና ትልቅ ክብር ስለሚሰጠው፣ የታላቁ (የቦረና) ልዩ ክብር Boorenticha በሚል በዓል ያከብርለታል፡፡*[34] *ከኦሮሞ ሥርዐቶች፣ መንፈሳውያት ጉባኤያትና ሥርዐተ አምልኮዎች ሁሉ፣ የቦረና ልዩ ክብርና ተሰሚነት አለው፤ ቦረና በኩር ነውና የዋቃና አያና ልዩ ስጦታዎች በዋናነት ለትውልድ የሚተላለፉት በእርሱ በኩል ስለሆነ፡፡ በበዓሉ ዕለትም የሚለበሱት አልባሳት የዋቃ ምሳሌነት በሚሰጠው ጥቁር ቀለም (ጥለት) ያጌጡ ልብሶች (የወንዱ ቡሉኮ እና የሴቷ ቆሎሳባታ የሚባሉ) ሲሆኑ ለሥርዓቱ የሚታረደው ኮርማም እንዲሁ ጥቁር ነው፡፡*[35] *የብኩርና ቦታ (ክብር) ምን ያህል እንደሆነ በኦሪት ውስጥም የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ከአባት ቀጥሎ የቤቱ ሓላፊ፣ ከርስት ሁለት እጅ የሚወርስ፣ የቤት ክህነት እሴቱ፣ የቤተ መንግሥትም አልጋ ወራሽ ነው (ዘፍ.25፡31፤ ዘዳ.21፡17፤ 2ዜና.21፡3)፡፡*

**Maarama (ማራማ)**:- *ኦሮሞዎች የቅዱሳንን ስም በሚመስሉ ስያሜዎች የሚያከብሯቸውም በዐላት ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንደኛውና ዋነኛው ‹‹ማራማ›› ሲሆን በዓሉ የሴቶች ነው፤ ወንዶች አይካፈሉበትም፡፡ በእናት መሪነት ስለሚከናወን እና የሴቶች በመሆኑም ‹‹አቴቴ›› ይባላል፡፡*[36] *ወንዶች ለምን በዓሉን እንደማይካፈሉ ሲጠየቁ ‹‹እነርሱ የማራማን ጣዕም የት ያውቁና፣ አምጠው አያውቁ!›› በሚል ጉንተላ ይመልሳሉ የብሔረሰቡ አዛውንት፡፡*[37] *ማራማ የወላድ አያና እንደመሆኑ መጠን*[38] *በዚህ በዓል ላይ የሚለማመኑት በዋናነት ልጅ መስጠትም ሆነ መንሳት የሚቻላት ማራማን ነው፡፡ እንዲያውም ሴት ስትወልድ* "baga Maaramiin si hiikte" *ይባባላሉ፤ በጥሬ ትርጉሙ ‹‹እንኳን ማርያም ፈታችሽ›› ማለት ነው፡፡ እንደ እነርሱ እምነት ማርያም ፈቅዳ ስለምትፈታ ነው እንጂ እርግዝና (ምጥ) ከባድ እስራት ነው፡፡ እንዲህ ባለ በዓል ከተማጸኗት ትፈታለች፣ አለበለዚያ እስራቱን ወደ ሞት ትቀይረዋለች፡፡ ስለዚህም አስፈላጊው ‹‹ጸበል ጸዲቅ›› ከተዘጋጀ በኋላ ዘካሪዋ እናት እንደ ዝክረ ሰንበቱ ሁሉ* "Maaramaaf nan dhaapha" *(‹‹ለማርያም ቆሜአለሁ››) ስትል ሌሎች ሴቶች የተሾመችውን ምንቸት ዙረው ይቀመጡና* "Maaramiin siif ha dhaabattu" *(ማርያም ትቁምልሽ) ይሏታል፡፡ ከዚያም ቀልጦ በተዘጋጀው ቅቤ ውስጥ ሰርዶ እየነከረች፤ ልጆችን ጨምሮ በሁሉም ግንባር ላይ ታስነካለች:- ይህንን* "mijuu" *(ሚጁ) ይሉታል፡፡ ስትባርካቸውም:-* "guddadhu, adda jabaadhu, of-koli" *ትላለች፤ በጥሬ ትርጉሙ ‹‹እደግ፣ ግንባረ ጠንካራ ሁን፣ እንክን አያግኝህ›› ማለት ነው፡፡*[39] *በዚህ መልክ ከበሉና ከጠጡ በኋላ ማራማን በዜማ ያመሰግኗታል፡፡*[40]

**Mabaachii (ማባቺ)**:- *በቅዱስ መጽሐፍ አስተምሕሮ መሠረት መባቻ የሚባለው ፀሐይ ልክ ስትገባ፣ ጨረቃ ተወልዳ በከፊል የምትታይበት ቀን ነው፡፡ ይህም የወር መጀመሪያ ቀን ነው፡፡*

---

33 ቦረና እና ባሬንቱ ‹‹ወንድማማቾች›› ሳይሆኑ በምዕራብ እና በምሥራቅ አቅጣጫ ተከፍለው የሰፈሩ ብሔረሰቡ‹‹ቡድኖች›› ናቸው የሚሉ አንዳንድ መላምቶች አሉ *(BATO፣ P.93)*፡፡ ያም ሆነ ይህ ቦረና የባሬንቱ ‹‹ታላቅ›› መባሉ ግን ብሔረሰቡ ዘንድ ቅቡል ነው፡፡

34 ታሲሳ እና ማርሳን፣ ገጽ 9፡፡

35 ዝኒ ከማሁ፡፡

36 Dirribii Damusee Bokkuu; Ilaalcha Oromoo፡ *Barroo Aadaa, Seenaa fi Amantaa Oromoo* (Finfinnee, Maxxansa 2ffaa, Hagayya, 2009), p. 119.

37 ወ/ሮ ሀንጋሬሼ (ቃለ መጠይቅ)፡፡

38 ታሲሳ እና ማርሳን፣ ገጽ12 ፡፡

39 ወ/ሮ ሀንጋሬሼ (ቃለ መጠይቅ)፡፡

40 ጀቤሣ፣ ገጽ 104፡፡

ቀኑም የተቀደሰ ነው (መዝ.80፡3)፡፡ እንዲያውም አይሁድ ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው የአምልኮ ግንኙነት ይልቅ መሰል በዓላትን ማድመቅ ያስበልጡ ስለነበር እግዚአብሔር ‹‹መባቻችሁንና ሰንበቶቻችሁን ነፍሴ ጠልታለች...›› በማለት አስጠንቅቆአቸዋል (ኢሳ.1፡14) ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም «...ስለ ወር መባቻ ማንም አይፍረድባችሁ» በማለት ለአማናዊቷ ዕረፍት ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ የተበየኑ በዓላት የድኅነት እንቅፋት እንዳይሆኑ አስረግጦ ተናግሯል (ቆላ.2፡16) ፡፡ እነዚህ ሁሉ አይሁድ ምን ያህል በተለይ መባቻን በትኩረትና በጥንቃቄ ያከብሩት፣ ከምንም በላይ ይጨነቁለት እንደነበሩ የሚያመላክቱ ነገሮች ናቸው፡፡

በኦሮሞዎች ዘንድም ‹‹ማባቺ›› የወራቸው መጀመሪያ ነው፤ በልዩ ሁኔታም ይከበራል፡፡ ለምሳሌ፡- በዕለቱ ወደ ሌላ የሚሔድ ዕቃ፣ ብር፣ እህል ወዘተ ውጭ ያድራል፤ እቤት ካደረ በማባቺ ወደ ሌላ መሔድ ክልክል ነውና፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከውጭ የሚመጣ ሰው (እንግዳ) ቢኖርም የቤቱን እህል የማይቀምስባቸው ቦታዎች አሉ፤ በእነርሱ አባባል ‹‹ባዕዳን ናቸውና አይገባቸውም!››፡፡ በብሉይ ኪዳን ከአሮን ልጆች በቀር ለሌሎች ያልተፈቀደ መብል እንደነበረ (ዘፀ.29÷33)፣ ለእስራኤላውያን ብቻ የተፈቀደው የፋሲካ መሥዋዕት ‹‹ከእርሱ ባዕድ ሰው አይብላ›› እንደተባለው ሁሉ (ዘፀ.12፡43)፡፡

Ingiccaa (**እንግጫ**):- ይህ የልጃገረዶች በዓል ሆኖ የሚከበረውም በዓመት አንዴ በመባቺ ቀን ላይ (የዘመን ወለወጫ፣ የወር መጀመርያ ቀን) ነው፡፡ ምንም እንኳን የኦሮሞ ዘመን መለወጫ ከመስከረም ጥቂት ቀደም ብሎ (ነሐሴ አጋማሽ አከባቢ) ቢሆንም፤ ይህ በዓል የአዲስ ዓመት መቀበያ ነውና የዚህ ደስታ ማብሰሪያ ቄጤማ በልጃገረዶች አማካይነት የሚታደልበት ቀን ነው፡፡ ከዚህ በዓል በፊት የጳጉሜን አምስት ቀናት በኦሮሞም ዘንድ የታወቁ ናቸው፡፡[41]

በዕለቱ ልጃገረዶች አምረውና ደምቀው የተገመደውን እንግጫ በመያዝ በአንድ ላይ እየዘፈኑ በየቤቱ እየዞሩ አበባና የቀጤማ ጉንጉን ያድላሉ፤ ልዩ ግብዣም ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህች ቀን ማንም እነዚህን ልጃገረዶች ሊያስቀይም አይሞክርም፤ እነርሱ በዕለቱ ‹‹ቅሩባነ እግዚአብሔር ናቸው›› ተብሎ ስለሚታመን ቢራገሙም ቢመርቁም ፈጥኖ ይሰማላቸዋልና! እንዲያውም የሚገርመው ለረጅም ጊዜያት ልጅ አጥተው የኖሩ ካሉ ልጃገረዶቹ ሲመጡ ይሳሉላቸውና ‹‹ይስማሽ›› ከተባሉ ይወልዱ እንደነበር በእርግጠኝነት የሚናገሩ አሉ፡፡

እዚህ ላይ ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ ማባቺ እና ይህ በዓል በአንድ ቀን መግጠማቸው ምን ያሳየናል? በቄጤማ ማብሰር ታጅቦ የሚከበረው ይህ በዓል ከጥፋት ውኃ መጉደል ብሥራት ጋር (ዘፍ.8÷11) ይናበብ ይሆን? የልጃገረዶች በዓል መሆኑ (በዘፈናቸው መድመቁስ) ከወለተ ሄሮድያዳ ታሪክ ጋር ላለመገናኘቱ ምን ማረጋገጫ አለ? (ማቴ.14፡6)

Garanfasa (**ገረንፋሳ**):- ገረንፋሳ ስያሜው ከምን እንደመጣ ለማብራራት ይከብዳቸዋል ፤ ብቻ ቀኑ በማባቺ አምስተኛ ቀን ላይ እንደሆነ ሁሉም ይስማሙበታል፡፡ ለምሳሌ፡- ማባቺ ዓርብ ከዋለ ገረንፋሳ ማክሰኞ ይውላል ማለት ነው፡፡ ይህ በዓል በዋናነት ለሕፃናት ጤንነት፣ ለጥጃና ለላም መፋፋት እንደሚከበር የሚናገሩ አሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚያደርጉት በዚህ ዕለት ላሞች እንኳ የማይታለቡ (ጥጆች በነጻ የሚጠቡበት) ቀን መሆኑን ነው፡፡ በዕለቱ እርሻም ሆነ ሌላ ሥራ አይሠራበትም፤ የግዝት በዓል መሆኑ ነው፡፡ በዓመት ውስጥ በሰባት ወር አንዴ ገረንፋሳ እና ሳናባታ የሚደራረቡበት ሁኔታ ስለሚፈጠር፤ በእርድ እንደሚከበር አዛውንቱ ይናገራሉ፡፡ ይህ ተጨማሪ ጥናት ቢጠይቅም ቢያንስ ከሚከበርበት ቀንና ከስያሜው መመሳሰል የተነሣ የኦሮሞ ገረንፋሳ ‹‹ገብረ መንፈስ ቅዱስ›› እንደሆነ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይገምታል!

41 ዝኒ ከማሁ፡፡

**Miikaa'ela (ሚካኤላ)** :- ሚካኤላ ደግሞ በገረንፋሳ ሳምንት ይከበራል (የማባቺ ዐሥራ ሁለተኛ ቀን መሆኑ ነው)፡፡ በየወሩ ቀለል ባለ ሁኔታ ከሚከበረው በተጨማሪ በዓመት ሁለት ጊዜ (ማለትም የኅዳር እና የሰኔ ሚካኤላ) በልዩ ዝክር (በእርድ) የሚከበሩ በዓላት ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ‹‹ሚካኤላ ማን ነው ለምንስ ይከበራል ለምንስ የኅዳርና የሰኔ ቀናቱ የተለዩ ሊሆኑ ቻሉ ለሚሉት ጥያቄዎች የአዛውንቱ ምለሽ "qooda isaati" ‹‹ሥርዐቱ ነው›› ወይም "duruu kan ture dha" ‹‹ከጥንትም የነበረ ወግ ነው›› በሚል ይቋጫል፡፡ ያም ሆነ ይህ ሚካኤላ ‹‹ሚካኤል አይደለም›› ብሎ የሚከራከር ካለ፤ ለምን በጋራንፋሳ ሳምንት ይከበራል? የኅዳሩና የሰኔውስ ለየት ተብሎ መከበሩ ለምንድን ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

**Madina (ማድና)** :- ለኦሮሞ ማዲና ሰብሎችን ከመብረቅ፣ ከዐውሎ ነፋስና ከበረድ የሚጠብቅ አምላክ ነው፡፡ ስለዚህም (በግምት ነሐሴ አጋማሽ አከባቢ) ገበሬው ገንፎ በቅቤ አዘጋጅቶ ይዞ በየማሳዎቹ ይዞርና እንደ ወጉ እየቆነጣጠረ ከወረወረባቸው በኋላ በአንድ ጥላ ሥር ተቀምጦ ‹‹ተረፈ መሥዋዕቱን›› ይበላል፡፡ እርድም የሚካሔድበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ በአንዳንድ ቦታዎች ‹‹ማራማ ሀጋያ›› (የነሐሴ ማርያም) እየተባለ ይከበራል፡፡[42] ዋናው ዓላማ ሰብሉ ያለ ምንም ችግር በዝናብ በቅሎ፣ በፀሐይ በስሎ ወደ ጎተራ ይገባ ዘንድ መማጸን ነው፡፡ ስለዚህም ከመዲና ቁጣ ለመዳን የግድ ይኸን በዓል ማክበር ያስፈልጋል፤ በዕለቱ ምንም ዓይነት ሥራ አይሠራም፡፡ ጉዳዩ በተጨማሪ ምርምር መረጋገጥ ቢኖርበትም ማዲና የሚለው ቃል ‹‹መድኅን››፣ ‹‹መድኃኔ ዓለም›› ከሚሉት ጽንሰ አሳቦች ጋር ተያያዥነት እንደሚኖረው ይገመታል፡፡

**Taaboree (ታቦሬ)** :- ታቦሬ በዋናነት የእረኞች (የወንዶች ልጆች) በዓል ነው፡፡ ሐጋያ በሚባለው (ነሐሴ) ወር ውስጥ የሚከበር ነው፡፡ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በአንድነት ይሰበሰቡና በእርጥብ አጠና፣ ጊዜያዊ ጎጆ ይቀልሳሉ፡፡ በጎጆው ፊት ለፊትም ትንንሽ እርጥብ እንጨት ያቆሙና በወጉ ተሰናድቶ እስከ ጎጆአቸው ከሚመጣላቸው ጎንፎ፣ ቅቤ፣ ጠላ፣ ወተት፣...በማፍሰስ ‹‹የፈጠርከን አምላክ አሳድገን፣ ለወግ ለማዕረግ አብቃን›› ብለው ዲጸልዩ፣ ሲበሉና ሲጠጡ ይውላሉ፡፡[43]

እስካሁን ድረስ እንዳየናቸው በዓላት ሁሉ ለምን ታቦሬ ተባለ? ለምንስ ይከበራል? ለምን በዳስ ውስጥ ሆነ? ለሚሉ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ማግኘት አልተቻለም እንጂ ብዙ ያልተገለጡ ነገሮችን ማገናዘብ ይቻላል፡፡ ያም ሆኖ ይኸ ግን ስያሜውም ሆነ አጠቃላይ ሥርዐቱ የሚያስታውሰን ነገር ይኖረዋል፡፡ በብሉይ ኪዳን እህል ከተከማቸ በኋላ የእስራኤል ልጆች ሰባት ቀን በዳስ ውስጥ ተቀምጠው አምላካቸውን ያመሰግኑ ነበር፡፡ ይህ በዓል *በዓለ መጸለት* ይባል ነበር (ዘሌዋ.23፡33-43፤ ዘኁ.29፡12-40)፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ስያሜው፣ የእረኞች በዓል መባሉ፣ በነሐሴ ወር እና በዳስ ውስጥ መከበሩ ምስጢረ መለኮት ገሐድ የሆነበትን ዕለት (በዓለ ደብረ ታቦርን) ያስታውሰናል፡፡

**Addaam (አዳም)** :- ለዚህ ጥናት ማጠናቀርያ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አዛውንት ‹‹አዳም›› የሚባል የኦሮሞ በዓል መኖሩን እንጂ የስያሜውን የት መጣ፤ እንዲሁም የመከበሩን መነሻ በውል አያስረዱም፡፡ ባላንበራስ ጀቤሣ ግን በመጽሐፋቸው ላይ ‹‹ኦሮሞዎች እግዚአብሔር የመጀመርያውን ሰው አዳምን እንደፈጠረና ሰው ሁሉ ከእርሱ እንደመጣ ያምናሉ፡፡ ስለዚህም ‹አዳም› ብለው በስሙ የሚያከብሩት በዓል አላቸው›› ሲሉ ገልጸዋል፡፡[44] የባላንበራስን አሳብ እውነት የሚያደርገው ደግሞ ብሔረሰቡ አባላት በዓሉን የሚከበርበት ጊዜ (ዕለት) ነው፡፡

---

[42] Dirribii, p. 120.

[43] ጀቤሣ፣ ገጽ 107፡፡

[44] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 101፡፡

*አዳምን የሚያከብሩት በጸሎተ ሐሙስ ሳምንት (ከፋሲካ ቀጥሎ ባለው ሐሙስ) ነው፡፡ ‹‹በአጋጣሚ ተገናኝቶ›› ካልተባለ በቀር፤ ይህ ዕለት ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ከሚከበረው የአዳም በዓል ጋር አንድ ቀን የሚውል ነው፡፡ ይህም ብሔረሰቡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ከማንም የተሻለ ስለ ክርስትና እና በዓላቱ ግንዛቤ እንደነበረው ፍንጭ የሚሰጥ ነው፤ ዛሬም ድረስ አሻራው አልጠፋምና፡፡*

**Gannii (ገኒ) :-** *ይህ የከብቶች በዓል ሲሆን፤ ‹‹ማራማ ሎኒ›› ተብሎም ይጠራል፡፡ በዋናነት የሚከበረውም በታኅሣሥ ወር ውስጥ ሲሆን፤ አንዳንዶች ጊዜውን ኅዳር ውስጥ ያደርጉታል፡፡*[45] *የበዓሉ መከበር ዋና ዓላማ ከብቶችን ፈጥሮ ለሰጣቸው አምላክ ምስጋና ለማቅረብ እና ከብቶች እንዲረቡ፣ ሟርት እንዳያገኛቸው፣ እንዳይቀጭጩ፣ ወዘተ. ለመመረቅ ነው፡፡*

*በዕለቱ አዲስ የከብቶች በረት በሰፊው ይሠራና በለምለም ቅጠል ዙሪያው ይሸፈናል፡፡ በበረቱ መሓልም እርጥብ እንጨት እንዲቆም ይደረጋል፡፡ ገንፎም በበረቱ ውስጥ ይገነፋል፡፡ ከብቶች ያለ ወትሮአቸው በቀን ይመጡና በተዘጋጀው የሐረግ መሹለኪያ በኩል አልፈው ወደ በረታቸው ይገባሉ፡፡ በየዓይነቱ ከሚዘጋጀው መብልና መጠጥ በመጠኑ በበረቱ መሓል በቆመው እርጥብ እንጨት ሥር ያኖራሉ፡፡ በከብቶቹም ላይ «መመረቂያ» የቀለጠ ቅቤ ይረጭባቸዋል፡፡ ከዚያም የተረፈውን እየበሉና እየጠጡ ከብቶችን የሚያወዳድሱ (ለእነርሱ ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር የሚገልጡባቸው) ዜማዎችን እየተቀባበሉ ያዜማሉ፡፡*[46] *ለመሆኑ ከብቶች ለምን በዓል ይከበርላቸዋል?/ ለምን የከብቶች በዓል ሆነ? ለምን «ገኒ»ስ ተባለ? ጊዜው ታኅሣሥ መሆኑስ ምን ያመለክታል? ገንፎውና እርጥቡ እንጨት በበረቱ መካከል የሚቀመጡትስ ለምንድን ነው? የሚሉት በአንክሮ ሊጤኑ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስያሜውና በዓሉ ከጌታ ልደት ጋር ይገናኝ ይሆን? ለሚለው መላምት ግን በዚህ ጥናት መልስ አልተገኘም፡፡*

## ፬.፬ ጸሎትና ምልጃ

**Galma /ገልማ/፣ Waldaa /ዋልዳ/ :-** *ይህ የኦሮሞዎች ‹‹የተለየ›› የጸሎት ቦታ ነው፡፡ ይህም የመንፈሳዊ ክብረ በዓልና የስግደት ማድረጊያ ቦታ ሲሆን የሚቆረቆረውም በአምባ ጫፍ ላይ ወይም በርካታ ትላልቅ ዛፎች እጅብ ብለው በበቀሉበት ውስጥ፣ ወይም በጅረቶች አከባቢ ወይም በትላልቅ ተራራዎችና ቋጥኞች (አለቶች) አከባቢ ወዘተ ነው፡፡*[47]

*በትላልቅ ዛፎች አከባቢ የሚደረገው ሥርዐተ አምልኮ ብሔሩ ቅድመ ታሪክ /የዘላንነት ሕይወት እና ኦዳ/ ጋር የተያያዘ እንጂ ዛፉን የማምለክ ምልክት አይደለም፡፡*[48] *በአንዳንድ ቦታዎች ዛፎች ብቻ ባሉበት የሚከናወን ሲሆን፤ በሌሎች ዛፎቹ እንደ አጸድ ብቻ ይሆኑና በእነርሱ የተከበበ ሌላ የማምለኪያ ቤት (ቤተ ጸሎት) ይሠራል፡፡ በቤት መልክ ከሚሠራው ባሻገርም በጫካ ውስጥ የተለየ ሥፍራ ለይተው በማጠር፣ በመካከሉ ትላልቅ ድንጋዮች በማቆም የሚጸልዩበት ሁኔታም አለ፡፡ ይህንን ቦታ «ሲዳ» በማለት ይጠሩታል የተከበረ የአምልኮ ሐውልት እንደማለት ነው፡፡ ምናልባት ይህ ሁኔታ የፍኖተ ሎዛውን የአባታችን ያዕቆብ «ቤቴል» ታሪክ ያስታውሰን ይሆናል (ዘፍ.28÷10-22)፡፡*

*ሌላው የሚገርመው ጉዳይ በእነዚህ የአምልኮ ሥፍራዎች ዙርያ የሚገኙ እንጨቶች ፈጽሞ አይቆረጡም፡፡ ልክ እንደ ቤተ ክርስቲያን አጸድ ማለት ናቸው፡፡ በተጨማሪም በውስጥ የሚያድሩ፣ በዙሪያቸው የተኮለኮሉ አራዊት እንዲታደኑ (እንዲገደሉ) አይፈቀድም፤ ለእነርሱ እነዚህ ‹‹አውሬዎች›› ሳይሆኑ ‹‹አዋይ›› ናቸው፡- የሥፍራው ክብር መገለጫዎች/የበረከት ምንጮች እንደማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን መሰል የአምልኮ ሥፍራዎች የተለመዱ እንደነበሩ የሚያመላክቱ ትውፊት አሉ፡፡ እሥራኤል ወገን ያልሆኑ ሥፍራዎች እና ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጫ ሥፍራዎችም ተደርገው ተጠቅሰዋል፡፡/ዘዳ.12÷2-4፤ዘፍ.18÷1፤ ዘፀ.24፡12-18፤ ዘዳ.32፡2፤ መዝ.46፡2:: /*

***ሥርዐተ ጸሎት*** **፡-** ብሔረሰቡ ስለ እግዚአብሔር ያለው አመለካከትና የእምነት ጥልቀት (*መሠረተ እምነቱ*) ከሚመዘንባቸው ነገሮች አንዱ ሥነ ቃል ነው፡፡ በምሳሌነትም አባቦኩዎች (*የብሔረሰቡ ሃይማኖት መሪዎች*) እና ሕዝቡ በኅብረት እየተቀባበሉ የሚዘምሩትን የጸሎታቸውን ይዘት እንደሚከተለው እንመልከት፡-[49]

---

[45] Dirribii, p. 119.

[46] ጀቤሣ ፣ ገጽ 108፡፡

[47] በኃሮ፣ ገጽ 32፡፡

[48] ጀቤሣ፣ ገጽ 100፡፡

[49] ዝኒ ከማሁ" ገጽ.95-97፡፡

| | |
|---|---|
| **Ya Rabbi Tokkicha...** | **አንዱ እግዚአብሔር ሆይ!** |
| Kan siin uume hin jiru | አንተን የፈጠረ የለም፤ |
| Siin malees kan uumame hin jiru | ያለ አንተም የተፈጠረ የለም፤ |
| Ruuda fi lafti uumaa harkakeeti | ሰማይና መሬት የእጆችህ ፍጥረት ናቸው፤ |
| Namnis, horiinis... | ሰውም፣ ከብትም... |
| Midhaan, bishaani fi qilleensis... | እህልም፣ ውኃም፣ ነፋስም... |
| Tolluuni fi muknis... | ተራራ እና እንጨት... |
| Kan garaadhaan munyuuqu... | በደረት የሚሳቡ ሁሉ... |
| Bineensi kotteen deemu... | በእግርም የሚራመዱ አውሬዎች ሁሉ... |
| Allaattiin baalleen kaattu uumaa harkakeeti | አዕዋፍም ሁሉ የእጆችህ ሥራ ናቸው፤ |
| Akka kalakeetti araara nuuf buusi. | እንደ ልብህ ጥራት ምሕረትን አውርድልን! |
| **Ya Waaqa Keenya!** | **አምላካችን ሆይ!** |
| Rabbi hundumaa uumte | ሁሉን የፈጠርከ እግዚአብሔር... |
| Dhiira fi dubartii goote | ወንድና ሴት አድርገህ... |
| Lafa diriirsite | መሬትን ዘርግተህ... |
| Tulluu muxxeessite | ተራራን አሹለህ... |
| Kan uumame hunduu suma harka | የተፈጠረ ፍጥረት ሁሉ በአንተ እጅ ነው፤ |
| Ijji sabakeetii waan argudha. | ይኸንንም ሁሉ የሕዝብህ ዐይኖች የሚያዩት ነው፡፡ |
| **Ya Rabbi Tokkicha!** | **አንዱ እግዚአብሔር ሆይ!** |
| Hin duutu, hin dulloomtu; | አታረጅም፣ አትሞትም፤ |
| Hin beeloftu, hin dheebottu; | አይርብህም፣ አይጠማህም፤ |
| Dukkanaaf dungoo hin baattu; | ለጨለማ ችቦ (መብራት) አትይዝም፤ |
| Aduuf dubaabo hin baattu; | ለፀሐይም ጃንጥላ አያሻህም፡፡ |
| Roobaan biqishita, | በዝናብ ታበቅላለህ፤ |
| Aduudhaan gogsita, | በፀሐይም ታበስላለህ፤ |
| Namaaf dabarsita. | ለሰውም ታሳልፋለህ (ትመግባለህ)፡፡ |
| Dhiiga mucaa goota; | ደምን አርግተህ ሕፃን ታደርጋለህ፤ |
| Hiika dhugaa goota. | በእውነትም ትገላግላለህ፤ |
| Duudaa dubbifta; | ዲዳ ታናግራለህ፤ |
| Qal'aa furdifta. | የከሣ ታወፍራለህ፡፡ |
| **Ya Waaqa Keenyaa!** | **አምላካችን ሆይ!** |
| Marga fi bishaan horiif uumte, | ሣርና ውኃን ለከብት ፈጠርክ፤ |
| Marga ilmaa lammiif, | ለምለም ልጅን ለወገኑ... |
| Horii, midhaan fi bishaan sabakeef. | ከብት፣ እህልና ውኃን ለሕዝቦችህ ፈጠርክ፡፡ |
| Xinnaa nuuf guddisi; | ትንሹን (ሕጻናትን) አሳድግልን፤ |
| Qal'aa nuuf furdisi; | የከሳን አወፍርልን፤ |
| Kan nuuf laatte nuuf eebbisi. | የሰጠኸንን ባርክልን፡፡ |
| **Ya Rabbi Tokkicha!** | **አንዱ እግዚአብሔር ሆይ!** |

| | |
|---|---|
| Adeemaa nagaan gashi; | የሂደን (መንገደኛ) በደህና መልስልን፤ |
| Beela'aa beela baasi; | የተራበን ከመራብ አድን (መግብልን)፤ |
| Dheebotaa dheebuu baasi; | የተጠማንም ከመጠማት፡፡ |
| Yaroo hundumaa siif sagadna; | ሁልጊዜ እንሰግድልሃለን፤ |
| Si sodaanna, si ulfeessina. | እንፈራሃለን፣ እናከብርሃለንም፡፡ |
| Waldaa keenya nuuf eebbisi; | የጸሎት ሥፍራችንን ባርክልን፤ |
| Bakka nagaa nu teessisi; | በሰላም አካባቢ አኑረን፤ |
| Diina unu irraa fageessi; | ጠላትን አርቅልን፤ |
| Jiruu fi jireenya nutti eebbisi; | ሥራችንንና ኑሯችንን ባርክልን፤ |
| Nagaa fi nageesso nuuf buusi; | ሰላምና ምህረትን አውርድልን፤ |
| Balaa diingataa nurraa fageessi; | ድንገተኛ መዓትን (መቀሰፍን) አርቅልን፤ |
| Kan nu jaallatu wajjin nu jiraachisi. | ከሚወደን ጋራ አኑረን፡፡ |
| **Ya Waaqa Keenya!** | **አምላካችን ሆይ!** |
| Hoofuu jennee siif saganna; | እግዚኦ ብለን እንሰግድልሃለን፤ |
| Siif jilbeeffanna; | ለአንተ እንንበረከካለን፤ |
| Addaan siif gombifamna; | በግንባራችንም እንደፋልሃለን፤ |
| Galata siif galchina. | ምስጋና እናቀርብልሃለንም፡፡ |
| **Ya Rabbi Tokkicha!** | **አንዱ እግዚአብሔር ሆይ!** |
| Kadhaa keenya nuuf dhaga'i; | ልመናችንን ስማልን፤ |
| Iddoo yaadnu fi iddoo abballuun nu ga'i. | ለምናስበውና ለምንመኘው አብቃን፤ |
| Kan siif laanne nuuf sooradhu; | ያቀረብንልህን (መሥዋዕታችንን) ተቀበልልን፤ |
| Lubbuu keenya nuuf qusadhu. | ነፍሳችንን ቆጥብልን (ዕድሜአችንን አርዝምልን)፤ |
| Ijoolleef nagaakee nuuf buusi; | ለልጆች ሰላምን አውርድልን፤ |
| Horata keenya nuuf eebbisi ...ameen! | ደክመን ያፈራነውንም ባርክልን...አሜን! |

**Caamsituu (ጫምሲቱ)** :- እነዚህ ብሔሩ ዘንድ እንደ ‹‹ልዩ ጸሎተኞች›› የሚታመኑ ሲሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች ዝናብ እንዳይዘንብ ሲፈለግ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው (ዝናብ እንዳይዘንብ የሚያደርጉ) ሰዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በመከር ወቅት እህል እንዳይበላሽ ፣ በሥርዓተ ቀብርና በሠርግ ዕለታት ሕዝቡ እንዳይረበሽ ሲባል ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ caamsituu (ጫምሲቱ) በቁሙ ሲተረጎም ‹‹ዝናብ የሚያቆም›› እንደማለት ነው፡፡ በእርግጥ እነዚህ ጫምሲቱዎች ምን ዓይነት ‹‹ጸሎት›› እንደሚጸልዩና ምን ዓይነት ድርጊቶች እንደሚያከናውኑ ግልጽ ባይሆንም ድርጊቱ ግን በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ከምናውቀው የነቢዩ ኤልያስ ተግባር ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንደሆነ እንረዳለን (1ነገ.17÷1-7፤ ያዕ.5÷17-18)፡፡

**Ayyaana Abbaa (አያና አባ)**:- ኦሮሞዎች በዐይን የማይታዩ ክፉና ደግ መናፍስት እንዳሉ ያምናሉ፤ ክፉዎቹ ቀሳፊዎች ሲሆኑ፤ ደጋጎቹ ደግሞ ጠባቂዎች (ዐቃብያን) ናቸው፡፡[50] ብሔረሰቡለሁለቱም መናፍስት መሥዋዕት ያቀርባል፡- ክፉዎቹ ተመግበው በያሉበት እንዲያርፉ (እንዳይተናኮሉ) ደጋጎቹ ደግሞ ለማደሪያነት በሚመርጧቸው ሰዎች አማካኝነት በዋቃ ቶኪቻ እና በሰዎች መካከል እንዲያማልዱ ለመለማመን ነው፡፡ *‹‹በተለይ ተገቢው መሥዋዕት በተገቢው ጊዜ የቀረበ እንደሆነ››* ይላሉ የብሔረሰቡ አዛውንት[51] *‹‹ወዲያ ወዲህ እየተክለፈለፉ አደጋ እንዳያደርሱብን ለለቃቸው ይቆጣጠራቸዋል፤ አለበለዚያ ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠናል ይላሉ፡፡››*

ከጸሎት በተጨማሪ በኦሮሞ ብሔረሰብ ዘንድ አጽዋማት የታወቁ ናቸው በሚጸሙባቸው ወቅቶችም ሰርዶ በራስ ማሠር፣ እሳት (ምድጃ) ሥር መተኛት፣ ወዘተ ሥርዐቶች የተለመዱ ናቸው፡፡ ይልቁንም ደግሞ ‹‹የጳጉሜን ጾም›› የታወቀች ናት፡፡ ግን ሁሉም የሚጾማት ሳይሆን በልዩ ምክንያት (በስእለት ሊሆን ይችላል) ከእነርሱ አዲስ ዓመት በፊት በቆሎ ብቻ የሚጾሙ አሉ፡፡[52] ከጸሎት እና አጽዋማት ተነጥሎ የማይታየው ሌላው ጉዳይ ስግደት ነውና የማይተዋወቁ የብሔረሰቡ አባላት ለመጀመርያ ጊዜ ሲተዋወቁ እንኳን ”ati sagadaa eenyuutii” (አንተ ሰጋጅነትህ /አባልነትህ የት ነው) መባባልን ያዘወትራሉ፡፡

***ሥርዐተ መሥዋዕት፡-*** *በኦሮሞዎች ዘንድ ‹‹መሥዋዕት›› የሚለውን ጽንሰ አሳብ የሚተረጉመው ‹‹አርሟ›› የሚለው ቃላቸው ነው፤ ይኸም በቀጥታ ሲተረጎም ‹‹ማጤስ›› እንደማለት ነው፡፡ በተለይ የኦሮምኛው ቃል ደም በማፍሰስ፣ ስብ በማጤስ ይፈጸም የነበረውን የኦሪቱን ሥርዓተ መሥዋዕት የመስዋዕቱን ያስታውሰናል፡፡ የመስዋዕቱን ሥርዓት በተለያዩ መገለጫዎች ለመመልከት እንሞክራለን፡-*

***(ሀ) Irreessa (‹‹ኢሬሣ››)(መሰዊያ)፡-*** *ኢሬሣ[53] የኦሮሞዎች መሠዊያ ነው፡፡ የሚዘጋጀውም ከተለያዩ መዓዛ ካላቸው እንጨቶች* (abbayii/ቀለዋ/፣ ulumaayii/ልምጭ/፣ kusaayee /ከሰይ/ *ሌላም ቅጠላቸው የለመለመና ያማረ ለጋ የሆኑትን) ቆርጠው በሐረግ አንድ ላይ በማሠር ነው፡፡[54] አንዳንዴም የተከበረ ድንጋይ በማቆም ሊሆን ይችላል፡፡ መሥዋዕት ሁሉ የሚቀርበው ወደዚህ ኢሬሣ የታረደውን እንስሳ ደም በመርጨት፣ ሥጋውን ከየብልቱ (የቀኝ ክፍል) ቆራርጦ በማስቀመጥ፣ እንዲሁም ከሁሉም ዓይነት እህል እየቆነጠሩ (በትንሹ እያነሱ) በማቅረብ ነው፡፡ ኢሬሣ የሚቀመጠው በዋናነት ለሥርዐተ አምልኮ በተለየ የጸሎት ቤት ወይም ተራራ ጥግ፣ ጥላ ባለው ትልቅ ዛፍ ሥር ወይም ከወንዝና ከምንጭ አጠገብ ነው፡፡ አልፎ አልፎ በእያንዳንዱ የእምነቱ ተከታይም ቤትም ሊኖር ቢችልም በሰዋራ ቦታ (‹‹ዲንቃ›› በሚሉት ጓዳ) መሆን አለበት፡፡ የኢሬሣው መቀመጫ የትም ቢሆን ማንም ሊደርስበት የማይችል ቦታ መሆን አለበት፡፡ ይህ የእሬሣው ቦታ ለእነርሱ ‹‹ቅድስተ ቅዱሳን›› መሆኑ ይሆን?!*

---

[50] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 190 ፡፡

[51] ወ/ሮ አንገራሼ ቡጢ (ቃለ መጠይቅ)፡፡

[52] ጀቤሣ ፣ገጽ 104፡፡

[53] በቁሙ ‹‹እርጥብ ሣር›› ማለት ሲሆን ጽንሰ አሳቡ ዛሬ ‹‹ኢሬቻ›› ተብሎ ከሚታወቀው ጋር መምታታት የለበትም፡፡ ‹‹ኢሬቻ›› በተለይ በዓመት ሁለት ጊዜ (መስከረምና ግንቦት አካባቢ) ለዋቃ ‹‹ምስጋና ማቅረቢያ›› የሚከበር የብሔረሰቡ በዓል ነው፡፡

[54] Dirribii, p. 93.

 © ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ማኅበረ ቅዱሳን

***(ለ) Dhiiga (ዲጋ) :-*** ይህ ‹‹ደም›› ማለት ሲሆን ዋነኛው የብሔሩ መሥዋዕት ክፍል ነው፡፡ ከሚበሉ እንሥሳት ሥጋ ብልቶችና የእህል ዓይነቶች ጋር ሆኖ በኢሬሣ (መሠዊያው) ላይ ይቀርባል፡፡ ትውፊት በኦሪት *‹‹የሥጋ ሁሉ ሕይወት ደሙ ነው፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያሥተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማሥተሰርያ ይሆን ዘንድ፣ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት* (ዘሌዋ.17÷11)፤ ከሚለው ጋር ተቀራራቢነት እንዳለው ማስተዋል ይቻላል በሐዲስ ኪዳንም *‹‹...በኦሪት ሕግ ሁሉ በደም ይነጻ ነበር፤ ደም ሳይረጭ ግን አይሰረይም ነበር›› (ዕብ.9፡22)* በማለት የተገለጸውን ስናነብ የኦሮሞ ባሕል መስዋዕት ለፈጣሪ ማቅረብ የተዘወተረ እንደነበር ማመሳከሪያ ይሆናል፡፡

በሌላ መልኩ እንኳንስ ሆን ተብሎ ለመሥዋዕት የታረደው ቀርቶ፤ ለሌላ ጉዳይ የሚታረድ እንስሳ ደም እንኳ ልዩ ዋጋ ይሰጠዋል፤ በተለየ ዕቃ ተደቅኖ በቤት መቃንና ጉበን እንዲሁም መሓል ምሰሶ ላይ እንዲረጭ ይደረጋል፡፡ ይህን መሰሉ ሥርዐት ከኦሪቱ ሞተ በኩር ለመዳን ይረጭ ከነበረው የእስራኤላውያን የፋሲካ በግ ደም ጋር ቁርኝት ያለው ይመስላል (ዘጸ.12÷1-14)፡፡ በእርግጥም አብዛኛዎቹ የብሔረሰቡ አባላት ለምን ደም በመቃን፣ በጉበንና መሃል ምሰሶ ላይ እንደሚቀቡ ሲጠየቁ ‹‹ቆዳሳቲ›› ከማለት ያለፈ ምላሽ አይሰጡም፤ ‹‹ሥርዐቱ ነው›› እንደማለት፡፡ መረጃ አቀባዮች የሥርዐቱን መነሻ እና ምክንያት አያውቁትም እንጂ ‹‹ሥርዐቱ›› ለመሆኑ (አስቀድሞ የኖረ ነገረ ግን ሊሻር የሚገባው እንዳልሆነ) ግን ጠንቅቀው ያውቃሉ፤ አስረግጠውም ያስረዳሉ፡፡ ባላምበራስ ጀቤሣ ግን ኦሮሞዎች ደጋግና ርኩሳን መናፍስት መኖራቸውን እንደሚያምኑ ከጠቀሱ በኋላ፣ በተለይ ለምን ደም የቤታቸውን መሓል ምሰሶ፣ የበራቸውን ግራና ቀኝ መቃን ላይ እንዲሁም ግምባራቸውንና ማንቁርታቸውን እንደሚያስነኩ ከአንዳንድ አዛውንት አገኘሁት ያሉትን ምላሽ (ምክንያት) እንዲህ ጽፈውታል፡-[55]

> *በምሰሶ ላይ የሚቀባው ደም ተጻራሪ መናፍስትን ከቤት ለማስወጣት (በቤት ውስጥ እንዳይኖሩ ለማድረግ)፣ በበር መቃን ላይ የሚቀባው ከውጭ ወደ ቤት እንዳይገቡ እንዲከላከል እንዲሁም፤ ግምባርና ማንቁርትን ደም ማስነካት "adda na jabeessi, lubbuu na dheeressi" (ግምባሬን አጠንክር፣ ዕድሜዬን አስረዝም) በማለት ርኩሳን መናፍስትን የማራቅ ዓላማ አለው፡፡›*
>
> *ዐፄ ልብነ ድንግል <u>እንደ ኦሮሞች ሥርዐት</u> የፈረሶቻቸውን ግንባር የቦረንቲቻ ደም እየቀቡ፣... <u>አምልኮ ባዕድ</u> አድርገው ነበርና....እግዚአብሔር ግራኝ መሐመድን አስነሳባቸው፡፡*

***(ሐ) Ixaana (ዕጣና):-*** የዕጣን መሥዋዕት በብሉይም ሆነ በሐዲስ የታወቀ ሥርዐት ነው (ዘፀ.30÷35፤ዘሌዋ.16÷12-13)፡፡ በኦሮሞዎች ሥርዐተ አምልኮ ውስጥም የዕጣን መሥዋዕት ዋነኛውና መደበኛው ነው፡፡ በኦሪት ከሊቀ ካህናቱ በቀር፣ ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛውን የክህነት ደረጃ ያለው ካልሆነ በቀር ዕጣኑን በጥናው ላይ እንደማያስቀምጥ ሁሉ በኦሮሞም ዘንድ የቃሉ መሪው እንጂ ‹‹ተራ›› ሰው በማጤሻው ገል ላይ ሊያስቀምጥ አይፈቀድለትም፡፡

***(መ) Daddarbaa (ዳዳርባ) እና Dhibaayyuu (ዲባዩ):-*** ‹‹ዳዳርባ›› በቁሙ ሲፈታ ‹‹መወርወር›› ማለት ሲሆን (ለሚበሉ ምግቦች የሚነገር) ‹‹ዲባዩ›› ደግሞ ‹‹ማፍሰስ/ጠብ ማድረግ›› የሚለውን ትርጉም ይይዛል (ለሚጠጡ ነገሮች የሚነገር)፡፡ እነዚህ ሥርዐቶች ለመሠዋዕት የቀረቡትን እህሎች ከየዓይነቱ ትንሽ፣ ትንሽ በመቆንጠር አልያም የተሠዋውን (የታረደውን) ከብት ብልት ከየዓይነቱ ፣ በመወሰድ በመሰዊያው ላይ መበተን (ማስቀመጥ) እንዲሁም ከየመጠጦቹ በትንሹ ማፍሰስ ነው፡፡

[55] ጀቤሣ፤ ገጽ 99፡፡

*በብሔረሰቡ እምነት መሠረት በዚህ መልኩ የሚሠዋለት መንፈስ በስውር መጥቶ ይመገበዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በቀጥታ ከኦሪቱ መስዋዕት ጋር የተገናኘ ነው፡፡‹‹የሚቃጠለውንም መሥዋዕት ይገፍፈዋል፤ በየብልቱም ይቆርጠዋል፡፡... የተቆረጡትንም ብልቶች...በእንጨቱ ላይ ይረበርቡታል...›› (ዘሌዋ.1÷6-8)*

*ሆኖ ተብሎ ለመናፍስት የሚሆን መሥዋዕት ተዘጋጅቶ ይቅርና የኦሮሞ ብሔረሰብ በዘወትር ኑሮውም ቢሆን አድባሩን፣ ቆሌውን ሳይለማመን ለእነርሱ የሚሆነውንም ትንሽ ነገር አስቀድሞ ቆርሶ ሳይወረውር፣ ቆንጥሮ ሳይበትን፣ ከሚጠጣውም ጨልፎ (ቀንሶ) ሳይደፋ ፈጽሞ ለራሱ አይቀምስም! ቡና ሲፈላ እንኳን ሴቷ የጀበናውን ክዳን ከፍታ* ”qaajabaa” *ይበሉ ትላለች፤ ‹‹ይመርቁ›› እንደማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ አባዋራው* "qaajabaa...Rabbi situ jabaa..." *(ኃይሉ አምላክ ስማን...) ብሎ ተገቢውን ‹‹ቡራኬ›› ከሰጠ በኋላ እንደተለመደው ቆንጥሮ ይወረውራል፤ ሴቷም ከቡናው በሲኒ ቀንሳ ትደፋለች፡፡ ይህንን ለምን እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ ምላሽን በአንድ ሥነ ቃላቸው ያጠቃልሉታል፡-* "kan nyaate nama hin nyaatu" *(‹‹የበላ ሰውን አይበላም››)፤ ባታበላው ግን ይበላሃልና የሚል መልእክት አለው፡፡*

***(ሠ) Haqa (ሐቃ):-*** *‹‹ሐቃ›› በዚህ አገባቡ ሲፈታ የከሳ፣ የመነመነ፣ ለማየት የማያስደስት ቁመና ያለው፣ የመናፍስት መሥዋዕት የሚለውን ይወክላል፡፡ ስሙም የተወሰደው ለዚሁ ሥርዐተ መሥዋዕት ከሚቀርቡ እንስሳት ሁኔታ ነው፡፡ መሥዋዕቱ በአሞራ እንጂ በሰው ስለማይበላ ከሲታ ገጽታ ያላቸው እንስሳት ተመርጠው ይሠዋሉ፡፡*

*ይህ መሥዋዕት የሚቀርበው ቤተዘመድ ከሆኑ (አንድ ‹‹የዘር ሐረግ›› ካላቸው) የብሔረሰቡ አባላት መካከል ሰው የሞተ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ‹‹አያና አባ›› (የአባታቸው መንፈስ) ተቆጥቶናል ብለው ስለሚያምኑ ‹‹የይቅርታ መጠየቂያ›› መሥዋዕት መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም በዕለቱ በግ አርደው በሜዳማ (ግላጭ) ሥፍራ ያስቀምጡና እነርሱ ተሰባስበው ራቅ ባለ ሰዋራ ሥፍራ ላይ በጸጥታ (ድምጽ ባለማሰማት) ይጠባበቃሉ፡፡ በዕለቱ እንስሳውም ሆነ ሰው (ከሕፃናት እስከ አዋቂ ድረስ) ማንም ቢሆን እህል ውኃ መቅመስ አይችልም፤ ገና ‹‹ዋቃ አልታረቃቸውምና››፡፡ ዋቃ እንደታረቃቸው የሚያውቁት ታርዶ የተጣለውን በግ ከሰማይ አሞራ መጥቶ የበላላቸው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ዕድላቸው ሁኖ ይህ ከተሳካላቸው ‹‹ታርቋቸዋልና›› እልልታው ይቀልጣል፣ ሌላ እንስሳ ታርዶ ይበላል፣ የአያናው ማወደሻ ዘፈን (‹‹ዳላጋ››) ይደምቃል፡፡*

*ይህ ሥርዐት (በተለይ የዋቃን እርቅ በሰማይ አሞራ መረዳት) ከኦሪቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በእሳት መውረድ ማረጋገጥ ጋር ያመሳስለዋል፡- ‹‹...እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጣ፤ በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት፣ ስቡንም በላ...›› (ዘሌዋ.9÷23-24)፤ ‹‹እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወረደች፤ የሚቃጠለውንም መሥዋዕት፣ እንጨቱንም፣ ድንጋዮቹንም በላች...›› (1ነገ.18÷38)፤ ‹‹...እሳት ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን ቁርባንና መሥዋዕቱን ሁሉ በላ...›› (2ዜና.7÷1) ተብሎ እንደተጻፈ፡፡*

***(ረ) Warajoo (ዋራጆ):-*** *በኦሮሞዎች ዘንድ ‹‹Warajoo›› የሚባለው የአንድን ሰው በደልና ሊመጣበት የሚችለውን መጥፎ ነገር ይሸከም ዘንድ የሚመረጥ እንስሳ ነው፡፡ እንስሳው እንደሰው አቅም ታይቶ ከብት፣ በግ፣ ፍየል አልያም ዶሮ ሊሆን ይችላል፡፡ እንስሳው ቀርቦ ባለ ዋራጆው እጁን በእንስሳው ላይ ጭኖ ይጸልያል (ዘሌዋ.1÷4) ወይም እፍ ይልበታል (ይተነፍስበታል)፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያ እንስሳ ይለቀቃል፡፡ ምንም እንኳን ሆን ተብሎ ለአውሬ ባይሰጥም የሰውየውን ጦስ ተሸክሟልና ቢሞት ወይም በአውሬ ቢበላ ባለ ወራጆው ሰው ‹‹የእንኳን ደስ ያለህ›› መግለጫ ይጎርፍለታል፤ ምክንያቱም ዋራጆው ‹‹ጦሱን ይዞ ሔዷልና!››፡፡ ከዚህ በኋላ (በእነርሱ እምነት) ይኽ ሰው አስቀድሞ የሠራው በደል ጠፍቶለታል፤ ወደፊትም ክፉ ነገር አያገኘውም፡፡ ምናልባት ይህ እንስሳ በቤት ውስጥ የሚታረድበት ሁኔታ ከተፈጠረ እንኳን እጁን የጫነበት (የተነፈሰበት) ባለወረጆው እንዲበላ አይፈቀድለትም፤ይህ ‹‹ከራቀው በደል ጋር መልሶ እንደመጋባት ነውና››፡፡*

በብሉይ ኪዳንም ኃጢአትን ለሠሩ ሰዎች ለማሥተሰርያ የሚፈጸም ሥርዐት ነበር፡- አውራ በግ፣ ጠቦት ወይም ወይፈን ላይ ካህኑ እጁን በመጫን የሰዎችን ኃጢአት ወደ እንስሳው ያስተላልፈዋል፡፡ ከዚያም እንስሳው ወደ በረሓ ተወስዶ ይለቀቃል፤ እንስሳውም የሕዝቡን ኃጢአት ሁሉ ተሸክሞ ‹‹ተቅበዝባዥ›› ይሆን ነበር (ዘሌዋ.16÷21-22)፡፡ ጌታችንም ‹‹እርሱ ግን በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤...›› የሚል ትንቢት የተነገረለት (ኢ.ሳ.53÷4)፣ ‹‹...እርሱ ስለ ኃጢአታችን በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ...እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና...›› የተባለውም (1ጴጥ.2÷24) በዚሁ አምሳል መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

## ፬.፰ ክህነት እና ሥርዐቱ

***Ayyaantuu* (አያንቱ) ወይም *Qaalluu* (ቃሉ) የኦሮሞ ‹‹ሌዋውያን›› :-** ስለ ቃሉ ምንነትና ተግባር አስቀድሞ ተገልጾአል፡፡ ኦሮሞዎች የቃሉ መንፈስ ማደሪያ እንዲሆን የተመረጠውን ሰው ‹‹አያንቱ›› (በቁሙ ሲፈታ ‹‹ዕድለኛ›› መንፈስ ያረፈበት፤ የተገለጠለት ማለት ነው)፣ ሉባ (ካህን) ወይም አባ የተቀባ “ሙዳ” [56] (የተካነ፣ የተሾመ) ብለው ይጠሩታል፡፡ እነዚህ ስለ መጻእያት ትንቢት በመናገር፣ እንደ አሳበ ዘመን ሊቃውንት በማገልገል፣ እንዲሁም በሕዝቡና በዋቃ መካከል ድልድይ በመሆን (መረጃ በማስተላለፍና በአማላጅነት) እንደሚያገለግሉ የሚታመኑ ናቸው፡፡ እንዲያውም ‹‹ቃሉ በክርስትናው እምነት ውስጥ እንዳለው እንደ ‹ጳጳስ› እና በእስልምናው ውስጥ እንዳለው እንደ ‹ኢማም› ዓይነት ተመሳሳይ ደረጃ ያለው፣ የሃይማኖትና የመንፈሳዊ ክብረ በዓላት አዋቂ የሆነ፣ ከአያና ውስጥ ከአንዱ ጋር ልዩና የጠበቀ ግንኙነት ያለው፣ በተወሰነ ወቅትም ይኸው አያና የሚሠፍርበት (የሚነግሥበት) ሰው ነው›› በማለት የገለጹ አሉ፡፡[57]

በዚሁ መሠረት በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱ በርካታ የብሔረሰቡ ባሕልና ሥርዐተ አምልኮዎች የሚተገበሩት፣ እስከ ዛሬም ድረስ ተጠብቀው የሚገኙት በቃሉ ዘንድ ነው፡፡ የሥርዐቱ ፈጻሚዎችም የቃሉ ማደሪያዎች (አያንቱ) ናቸው፡፡ ስለዚህም ቃሉዎች ለኦሮሞ ብዙ ነገር ናቸው፣ እንደ ነቢያት ትንቢት ይናገሩላቸዋል፣ እንደ ሊቃውንት ዘመኑን ይቆጥሩላቸዋል (መቁጠር ብቻም ሳይሆን እንደ (ጠንቋዮችም አዋቂዎች) በጎና ክፉ ቀናትን ይለዩላቸዋል)፣ እንደ ካህናት መሥዋዕት ያቀርቡላቸዋል፣ እንደ ቅዱሳንም ከዋቃ ጋር ያስታርቋቸዋል (ያማልዷቸዋል)፡፡

***‹‹አያንቱ›› ለመሆን የሚያበቁ ሁኔታዎች :-*** በዋናነት ሦስት ናቸው፤ የዋቃ ምርጫ፣ የሕዝብ የብቃት ምስክርነትና መገርዘ፡፡

**(ሀ) በዋቃ መመረጥ፡-** መሪዎቹ ‹‹አያንቱ›› (ዕድለኛ) የተሰኙትም ይህ ሥልጣን ያለ ዋቃ (እግዚአብሔር) ምርጫ የሚገኝ አይደለም ሲሉ ነው፡፡ በመሠረቱ ይህ ሁኔታ ለክህነት ከመመረጥ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ክህነት መመረጥን (መታደልን) እንደሚጠይቅ፣ ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉት ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል (1ጴጥ.2÷9፤ 1ቆሮ.12÷29፤ 1ጢሞ.3÷2-13፤ ቲቶ.1÷5-9)፡፡

**(ለ) ከሕዝቡ የብቃት ምስክርነት :-** የኦሪት ካህናት ‹‹ነውር ያለባቸው›› እንዳይሆኑ የሚመረጡበትን ቅድመ ሁኔታ እግዚአብሔር በዝርዝር ለሙሴ ነግሮታል (ዘሌዋ.21፡16-23)፡፡ በኦሮሞ ዘንድም ከሰማያዊው ዋቃ በተጨማሪ አያንቱ ለመሆን የሕዝብ ምስክርነት በእጅጉ ያስፈልጋል፡-[58]

---

[56] በመጽሐፍ ቅዱስ እና በጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ መሠረት አገርን የሚመሩ ነገሥታት በካህናት ተቀብተው እንደሚነግሡ እና መንበራቸውንም በቤተ ክህነት እውቅና እንደሚያጸኑ ሁሉ የኦሮሞ አባ ገዳዎችም (የገዳ አስተዳደር መሪዎች) ወደ አባ ሙዳዎች (የሃይማኖት መሪዎች) መጥተው ‹‹ቅዱስ ምግብ›› ተቀብለው ሥልጣናቸውን ያስመርቃሉ፤ ቃል ይገባሉ፤ ያጸናሉ፡፡ (Dirribii, p.248፤ BATO, P.47)

[57] በኃሮ፤ ገጽ 30፡፡ ቃሉ ለኦሮሞ የሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዐት ማከናወኛ ‹‹ተቋም›› ጭምርም ነው፡፡

[58] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 30-31፡፡

*ምንም እንኳን አብዛኛው የቃሉ የሓላፊነት ሥራ በዘር የሚተላለፍ ቢሆንም ፤ አንድ ሰው የቃሉ ማደሪያ (ኢያንቱ) ሊሆን የሚችለው የኢያናው መንፈስ በተጨባጭ እንደሰፈረበት (እንደነገሠበት) ሲያስመሰክር ብቻ ነው፡፡ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴውም ንጹሕና ምስጉን፣ ባሕላዊውን እርምት (taboo) የሚጠነቀቅ፣ «safuu» (ሳፉ) የሚሰኙ የሥነ ምግባር እሴቶችን (values) የሚጠብቅ፣ በየወቅቱ ያሉትን የእምነት ክብረ በዓላት የሚያከብር (የሚያስከብር)፣ በሚያደርጋቸውም ክንዋኔዎች ሁሉ እውነትን የሚከተል፣ ከኃጢአትም የራቀ መሆን አለበት፡፡*

(**ሐ**) **ግርዛት፡-** ኦሮሞ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ የግርዛት ባህል ቢኖረውም እዚህ ላይ ለማንሣት የተፈለገው ግን በብሔረሰቡ ዘንድ ብቻ የሚታወቀውን የግዝረት አፈጻጸም ነው፡፡ ለምሳሌ በብሔረሰቡ የገዳ ሥርዐት ውስጥ በሃይማኖታዊ መሪነት የሚሾሙት ሰዎች የተለያዩ ደረጃዎች ያላቸው ሲሆን ከመጀመርያው ደረጃ (ጋዳ አያና) ወደ ሉባ ለመሸጋገር በ40 ዓመታቸው መገረዝ ዋናው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡[59]

## ፬.፮ ስእለት እና ስጦታዎች

*(ሀ)* Qisfata (**ቅስፋታ**):-ቃሉ ባለባቸው የኦሮሞ ብሔሩ ዘንድ ዐሥራት፣ በኩራትና ቀዳምያት መስጠት የተለመደ ነው፤ ይህንን በጥቅሉ ‹‹Qisfata›› ይሉታል፡፡ በተለይ አዲስ እህል ሲደርስላቸው ራሳቸው ሳይቀምሱት አስቀድመው ወደ ቃሉ ወስደው በመስጠት ‹‹ያስባርካሉ››፡፡ ላምም የወለደችላቸው እንደሆነ የመጀመሪያውን ወተት አልበው ወደዚያ ሳይሰጡ ለራሳቸው የማይቀምሱ በርካቶች ናቸው፡፡ በኦሪትም እስራኤል ከሚሰበስቡት ምርት ሁሉ ለቤተ እግዚአብሔር እንዲወስዱ ታዝዘው ነበር (ዘዳ.26÷2)፡፡ ወቅታቸውን ጠብቀው ለሚከናወኑት ሥርዐተ አምልኮዎች ወደ ቃሉ ቤት ሲንቀሳቀሱም ተገቢውን ‹‹መባዕ›› መያዝ የተለመደ ነው (መባው ብዙውን ጊዜ በኑግ የተቀላቀለ ቆሎ፣ ዳቦ፣ ቡና፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል)፡፡

*(ለ)* Mataa Galchaa /*ማታ ጋልቻ*/ :- ኦሮሞዎች በተቸገሩ ጊዜ ወደ ዋቃ ቶኪቻ ሊያማልዱቸው ለሚችሉ ‹‹አማልክት›› ስለት ይሳላሉ፡፡ ይህም በቋንቋቸው ‹‹wareegaa›› (ዋሬጋ) ይባላል፡፡ ዋሬጋ ብዙውን ጊዜ የሚፈጸመው በቁስ አካል ስጦታ መልክ ስለሆነ የተለየ ነገር አይደለም፡፡

ከኦሮሞ ብሔረሰብ ስለት ውስጥ ለየት የሚለው ‹‹*Mataa Galchaa*›› *(ማታ ጋልቻ) የሚባለው ነው፤* በግርድፉ *ሲተረጎም ‹‹ራስን ማስገባት›› እንደማለት ነው፡፡ ይህ ሥ*ርዐት አንድ ሰው (ወንድ ወይም ሴት ሊሆን ይችላል) በተለያዩ ምክንያቶች ሲታመም ወይም ችግር ሲገጥመው ከዚህ ችግር ለመላቀቅ ይችል ዘንድ ወደሚያውቃቸው ቃሉዎች (መናፍስት) ይጸልያል፣ ይሳላል፡፡ ስእለቱ ደግሞ ‹‹mataa kiyya siif galcheera›› የሚል ነው፤ ራሴን አስገብቼልሃለሁ (ሰጥቼሃለሁ) ማለት ነው፡፡ ይህን መሰሉ ስእለት ምናልባትም ‹‹...እግዚአብሔር ከእኔ ጋራ ቢሆን... ወደ አባቴ ቤት በጤና ቢመልሰኝ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል›› (ዘፍ.28÷20-21) ብሎ እንደተሳለው እንደ አባታችን ያዕቆብ ያለ ‹‹ራስን መስጠት›› መሆኑ ነው፡፡

አንድ ራሱን ያስገባ (ተስሎ የሰጠ) ሰው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቋሚ የቃሉ አገልጋይ ይሆናል (ወንድ ከሆነ አፍአዊ ተግባራት ላይ በመሠማራት፣ ሴት ከሆነች ደግሞ ማይ በመቅዳት፣ ቡና በማፍላትና በመሳሰሉት የውስጥ ተግባራት)፡፡ ይልቁንም ደግሞ ራሱን ለ‹‹አምላኩ›› ለይቷልና ጠጉሩን አይላጭም፤ ቢላጭ ግን ይሞታል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሚመገባቸውም ምግቦች ‹‹የማያረክሱ›› መሆን አለባቸው፡፡

[59] ጀቤሣ፣ገጽ 39፡፡

አሁን ሙሉ በሙሉ የቃሉ ክልል ውስጥ በባለቤትነት ገብቷልና እንደ መንፈሱ ተሸካሚዎች ሁሉ ሬሣ ማየትም ሆነ መንካት አይፈቀድለትም፤ ስእለቱ ይበላሽበታልና! ከዚህ የስእለት ‹‹አጣብቂኝ›› መላቀቅ የሚችለው ከጥቂት ጊዜያት አገልግሎት በኋላ በቃሉው መልካም ፈቃድ በኮርማ ወይም በመሲና ላም ‹‹ልዋጭ›› (በመስጠት) ብቻ ነው፡፡

ይህ የኦሮሞዎች ‹‹ማታ ጋልቻ›› ከብሉዩ ‹‹ናዝራዊነት›› ጋር የተገናዘበ ይመስላል፡፡ *‹‹...ወንድ ወይም ሴት ለእግዚአብሔር ራሱን የተለየ ያደርግ ዘንድ ልዩ ስእለት ቢሳል ከወይን ጠጅና ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን የተለየ ያድርግ...ራሱን ለመለየት ስእለት ባደረገበት ወራት ሁሉ ራሱን አይላጭ፤...ወደ ሬሣ አይቅረብ...››* (ዘኁ.6÷2-6)፤ *‹‹...ልጁም (ሶምሶን) ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናልና በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት...››* (መሳ.13÷5) እንደተባለው፡፡

## ፬.፯ በእንተ ሙታን

**ስለ ሞት እና ሙታን ያላቸው እምነት፡-** በኦሮሞዎች አንዲት ተወዳጅ ብሂል አለቻቸው፡- "kan sodaatanis du'a, kan hin oolles du'a" የምትል፤ ‹‹የሚፈራ ሞት ነው፣ የማይቀርም ደግሞ እርሱው ነው›› እንደ ማለት ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያነጋገራቸው የብሔረሰቡ አረጋውያን (ሁሉም ማለት ይቻላል) ስለ ገነትና ሲዖል ግልጽ ባለ ሁኔታ አያስረዱም፡፡ ግን ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ በተዘዋዋሪ ቃላት ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሰው በሌሎች ላይ መጥፎ ነገር ሲሠራ ካዩ ‹‹ነፍሱን ለምን ለኩነኔ ይዳርጋል?!›› እያሉ ይገረማሉ፡፡ የሚችን ሰው ልጅም መበደል አይፈልጉም፡፡ ‹‹በሰማይ ትጠይቀኛለች›› ይላሉ፤ የሞቱት ይገናኛሉ የሚል እምነት ስላላቸው፡፡

> *ኦሮሞች በአካለ ትንሣኤ ያምናሉ፡፡ አካሉም ሲነሣ ከሕመም፣ ከሐዘንና ችግር ነጻ እንደሚሆንና አሁን ካለው አካል የበለጠ ፍጹም አካል እንደሚሆን፣ እንደገናም እንደማይሞት ያምናሉ፡፡ አንዳንዶቹም ከቤተሰባቸውና ከወዳጆቻቸው ጋር እንደገና ባልታወቀ ቦታ እንደሚኖሩና አንዳንዳቸው ደግሞ ያልታወቀ ቅጣት እንደሚደርስባቸው ያምናሉ፡፡*[60]

**‹‹ሬሳ ያረክሳል››፡-** ሁሉም የብሔረሰቡ አባላት ባይሆኑም ቃሉ በተስፋፋባቸው አከባቢዎች ለሬሳ ያለው አመለካከት የተለየ ነው፡፡ እንኳንስ *ሬሳ የነካ ቀርቶ በዐይኑ ያየ ሰው ‹‹ይረክሳል››* ተብሎ ስለሚታሰብ እስከተወሰኑ ቀናት ወደ ቃሉ ቤት እንዲገባ አይፈቀድለትም፡፡ ይህም ሁኔታ በኦሪት *‹‹የሞተውን ሰው በድን የሚነካ ሰባት ቀን ርኩስ ይሆናል...ባይነጻ የእግዚአብሔርን ድንኳን ያረክሳል...›› የተባለውን ያስታውሰናል (ዘኁ.19÷11-22)፡፡*

በተለይ ደግሞ የቃሉ መንፈስ ያረፈባቸው (አያንቱ የሚባሉት) ወደ ለቅሶ ቤት ፈጽሞ አይሔዱም፡፡ ምናልባት የሞተው ከዘመዶቻቸው ከሆነ እንኳን ወደ ሌላ ቦታ ያሸሹአቸዋል፤ አልያም በተለየ ቤት ይዘጋባቸዋል፡፡ አለበለዚያ መንፈሱ በከፍተኛ ሁኔታ ያስጨንቃቸዋል (ይታመማሉ)፤ ከባሰም እነርሱን ወደ አላሳፈላጊ ሁኔታ መርቶ ራሱ ሊርቃቸው ይችላል፡፡ በብሉይም ስለ ካህናቱ ቅድስና እንዲህ የሚል ተነግሮ ነበር፡-

> *‹‹...ከወገናቸው በሞተ ሰው ራሳቸውን እንዳያረክሱ...ስለሞተ ሰው ራሳቸውንና ጢማቸውን አይላጩ፣ ሥጋቸውንም አይንጩ፣... ወደ ሞተ ሰው ሁሉ አይግቡ...››* (ዘሌዋ.21÷1፣5፣11)፡፡

[60] ጀቤሣ (ገጽ 185) ቡሩስ የተባለው የውጭ ዜጋ ስለ ብሔረሰቡ ከጻፈው እንደጠቀሱት፡፡

እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች (በተለይ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ውስጥ) የእውቅ ቃሉ መንፈስ ተሸካሚዎች ሲሞቱ እንኳን ወደ ቤተ ክርስቲያን አይወሰዱም፡፡ አለመወሰዳቸው ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያኑ በተሻለ ሁኔታ መቃብር ቤት በስማቸው በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተንቆጥቁጦ (አምሮ) ተዘጋጅቶላቸው እያለ እነርሱ ሲሞቱ ግን ሬሳቸው እዚያው መንደር አከባቢ እንዲቀበር ይደረግና ለማስመሰል ያህል የታረደ በግ በሳጥን በሕዝብ ታጅቦ ይቀበራል ፡፡

**Qabbaneessaa (ቃባኔሣ)- ጸሎት በእንተ ሙታን:-** በብሔረሰቡ ዘንድ ለሟች ተዝካር ማውጣት የተለመደ ቢሆንም ከዋናው ተዝካር በፊት ቃባኔሣ ማድረግም የተለመደ ነው፡፡[61] ‹‹ቃባኔሣ›› በቁሙ ‹‹ማብረድ›› ማለት ሲሆን፤ ‹‹የሟች ነፍስ አብርድ›› ተብሎ የሚጸለይበት ሥርዐት ነው፡፡ በእርግጥ ‹‹አብርድ›› የሚባለው የሚተኩስ (የሚያቃጥል) ነገር ስላለ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም አብዛኞቹ ግን ይህችን ምስጢር በደንብ ማብራራት ይሳናቸዋል፡፡ ብቻ ሰዎች ተጠርተው የተደገሰውን ድግስ ከበሉና ከጠጡ በኋላ ‹‹ነፍሷ ይብረድ፣ነፍስ ይማር›› ብለው ይመርቃሉ፡፡

**Ekeraa (ኤኬራ)፡-** በኦሮሞዎች ዘንድ ነፍስ ‹‹ሉቡ›› የምትባል ሲሆን፤ ከሥጋ ስትለይ ግን ‹‹ኤኬራ›› ትባላለች፡፡ በብሔረሰቡ እምነት ደግሞ ይህችን የሞተች ነፍስ (‹‹ኤኬራ››) የሚያናግሩ፣ ከሕያዋን ቤተ ዘመዶቹ ጋር አገናኝተው ሳይጨርሷቸው የቀሩ ወይም ያልተጣሩ ጉዳዮችን መረጃ የሚያለዋውጡ ‹‹ekeera dubbiftuu›› አሉ፡፡ በዚህ መንገድ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ለዚሁ አገልግሎት በተመረጡ (ኢያንቱዎች) አማካኝይነት ‹‹ይናገራል›› ተብሎ ስለሚታመን ቤተ ዘመድ ተሰብስቦ ወደ መናፍስት ጠሪዎቹ ሔዶ ይጠይቃል፡፡

አስቀድሞ እንደተገለጸው በዚህ ሥርዐት ትልቁን ሥፍራ የሚይዘው ባሕላዊ እምነት ‹‹የሟቹ መንፈስ ተነሥቶ/መጥቶ ይናገራል›› የሚለው ነው፡፡ ይህ እምነታቸው በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ሲመዘን እውነትነት ያለው ይመስላል፤ የነቢዩ ሳሙኤልን ‹‹መንፈስ›› ታሪክ እናውቃለንና (1ሳሙ.28÷3-19)፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ቅዱስ መጽሐፍ ይህ ሊኖር እንደሚችል በማስመር እስራኤል በእንዲህ ዓይነት ተግባር አምላካቸውን እንዳያሳዝኑት አስጠንቅቋል (ዘሌዋ.19÷31፤ዘዳ.18÷11)፡፡

## ፬.፰ ቅድስና እና ንዋያተ ቅድሳት

**የሚያረክሱ/የተከለከሉ ነገሮች፡-** ኦሮሞዎች ‹‹ቅድስናን ያረክሳሉ›› የሚሏቸው ነገሮች አሏቸው፡፡ በኦሮምኛ ‹‹laguu›› ይባለል፤ ‹‹ክልክል›› ወይም ‹‹ሊራቅ የሚገባው›› እንደማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ከእነዚህ ነገሮች ‹‹ነጻ›› ካልሆነ በቀር ወደ አምልኮ ቦታዎች መግባት አይችልም፤ ‹‹ርኩስ›› ነውና! ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ብቻ በምሳሌነት ለመጥቀስ እንሞክር፡፡ ሬሳ ማየትና መንካት (አስቀድሞ እንደተገለጸው)፣ የተከለከሉ ምግቦችን መመገብ (በተለይ በቃሉ ዘንድ ከእንስሳት ፍየል[62]፣ ከዕፅዋት ደግሞ ተልባ፣ ሽንኩርት እና አንዳንድ ቅመማ ቅመም) ‹‹ያረክሳሉ›› ስለሚባሉ ክልክል ናቸው፡፡[63]

**Qumbii /ቁምቢ/ (የሲመት ‹‹ቅዱስ ምግብ››)፡-** የሚያረክሱ ምግቦች እንዳሉ ሁሉ የሚቀድሱም እንዳሉ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ በገዳ ሥርዐት (በተለይ በቦረና እና ጉጂ ኦሮሞ) አዲስ አመራር ሲመረጥ አዲሱ ካቢኔ ቁምቢ የሚባል ‹‹ቅዱስ ምግብ›› በአባ ሙዳዎች (ካህናት) አማካይነት እንዲበላ ተደርጎ እግዚአብሔርን እንዳያሳዝን፣ ፍርድ እንዳያጓድል ቃለ መሐላ ይፈጸማል፡፡ ምግቡ ከምን ዓይነት ነገር እንደተዘጋጀ ግን ከማክበራቸውና ከመፍራታቸው የተነሣ ሊናገሩ አልደፈሩም፡፡[64]

---

[61] ጀቤሣ፣ ገጽ 189፤ ወ/ሮ ሀንጋራሼ እና አቶ ቤኛ (ቃለ መጠይቅ)፡፡

[62] ፍየል ለምን ተለይታ እንደ ‹‹ርኩስ›› እንደተቆጠረች ብዙዎቹ በቂ አመክንዮ፡፡ ያላቸው አይመስሉም፤ አንዲት አዛውንት ብቻ ‹‹ፍየል የሰይጣን

[63] ንብረት ናትና›› ብለውኛል፡፡ ምናልባት ግን በወንጌላችን ላይ የኃጥአን ምሳሌ ሆና መነገሯን እናውቃለን፡፡ ይህ ግን ‹‹ርኩስ›› የሚያሰኛት አይደለም፤ ባህርይዋን በሚመሳሰል ግብር ለመግለጽ እንጂ ፍጥረተ እግዚአብሔርን ‹‹ርኩስ›› ለማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ሴቶች በወር አበባቸው ጊዜ፣ ወንድሞ ሆነ ሴት ደግሞ ሩካቤ ፈጽመው ወደ ቃሉ ቤት (‹‹ቅዱሳት›› ቦታዎች) መግባት፣ የተቀደሱ ዕቃዎችንም (እንደ ጫጩ፣ ካላቻ) መንካት እንደማይችሉ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያውቃል፤ ድርሳናትም ይገልጻሉ (Dirribii, p.86)፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጉዳዮች ብሔሩ አባላት ዘንድ እንደ ‹‹አይነኬ ጉዳዮች›› ስለሚቆጠሩ ደፍሮ ለመጠየቅ አልተቻለም፡፡

[64] አቶ ዋቴ (ቃለ መጠይቅ)፤ BATO (ገጽ.47)፡፡

**Hora /ሆራ/ (የኦሮሞ ‹‹ቅዱስ ውኃ››)፡-** በኦሮሞዎች ዘንድ ሆራ የመፈወስ ኃይል ያለው፣ ከሌሎች ውኃማ አካላት የተለየ የድኅነት ማግኛ የሆነ ፍል ውኃ (ሐይቅ) ነው፡፡ እንደ እነርሱ እምነት በዚህ ሐይቅ መነከር ለሰዎችም ሆነ ለከብቶች ፍቱን ‹‹መድኃኒት›› ነው፡፡ ይህ በክርስትናው ‹‹ጠበል›› መሆኑ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዶች የዛሬዎቹን የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋና ዋና የጠበል ቦታዎች (እንጦጦንና የዝቋላ አቦን ጨምሮ) ‹‹ተነጥቀው›› ነው እንጂ ጥንት የኦሮሞ ሆራዎች እንደነበሩ ጽፈዋል፡፡[65]

**«ንዋያተ ቅድሳት»** :- እነዚህ የብሔረሰቡ የክብር ዕቃዎች ሲሆኑ ‹‹ulfoowwan›› ይሏቸዋል፤[66] «የከበሩ» እንደማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ብቻ እንጥቀስ *Bokkuu* /ቦኩ (እንደ ኦሪቱ በትረ አሮን እና የጳጳሳቱ በትረ ሙሴ ያለ «ከከበሩ» እፅዋት የሚዘጋጅ «ቅዱስ» በትረ-ሥልጣን)ነው፡፡ *Kallacha*/ ካላቻ እግዚአብሔርን ለመለመን እና ከባድ እርቆችን ለመዳኘት የሚጠቀሙበት «ኮከባዊ» ብረት)፤ *Caaccuu* /ጨሌ (ከከብቶች ቆዳ ተሸንሽኖ የሚዘጋጅና ወላድ ሴቶች የሚይዙት የምሕረት ምልክት)፤ *Callee* /ጫሌ (በተለያዩ ኅብረ ቀለማት ያሸበረቀና የሴቶች ተፈጥሮ በልዩ ልዩ ጸጋዎች እንዳጌጠ የሚያመለክት ድቡልቡል ጌጥ ነው፡፡*Alangaa* /አለንጋ (ከጉማሬ ቆዳ የሚዘጋጅና የገዳ መመሪያዎች በጫፌ /ምክር ቤት/ ሲተላለፉ አልያም ለሕዝቡ ሲነገሩ ለማጽኛ እንደ ፍርድ ቤት መዶሻ የሚጠቅም መሣሪያ ነው፡፡ *Siinqee*/ሲንቄ ረዘም፣ ቀጥ ያለች፣ ቀጭንና አንጓ አልባ የሴቶች የክብር በትርቡ *Ciico/* ጪጮ ከቅል ወይም ከሸክላ በኅብረ ቀለማት አጊጦ የሚሠራ የወተት መያዣ፣ የወላድነትና የሠላም ምልክት የሚታመንበት የባልትና ዕቃ ሲሆን፣ በሴቶች ዘንድ ልዩ ክበር አለው፡፡Qanafaa/ቃናፋ (ከእንጨትና የተለያዩ ጌጣጌጦች የሚሠራ፣ በተለይ የአርሲ ወላድ ሴቶች ለውበትና ለክብር ከካላቻ ጋር በግንባራቸው የሚያስሩት ጌጥ ነው፡፡ /Hagannaa/ ሀጋና እጅግ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ኃራም የሆነ በአባ ገዳዎች ብቻ የሚታወቅ ለማየት ቀርቶ ስሙን እንኳን ለመጥራት የሚያስፈራቸው እንደ ‹‹ታቦት›› ነዋየ ቅድሳት ነው፡፡ አልባሳተ ‹‹ካህናት›› (ለዛሬው ኦሮሞ ሰንደቅ ዓላማ መነሻ እንደሆነ የሚነገርለት ጥቁር፣ ቀይና ነጭ ቀለማት ያለው የቃሉ ጥምጣም)[67] ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

**‹‹ቅዱሳት መካናት››** :- Gabalaa/ጋባላ (የገዳ አባቶች የሚሰበሰቡበት ቦታ ሆኖ ተለይቶ የሚታጠርና ጫማ ተደርጎ የማይገባበት፣ ‹‹በንጽሕናቸው›› የታወቁ ሰዎች ካልሆኑ ማንም የማይገባበት ‹‹ቤተ መቅደስ››) ነው፡፡ እንደዚሁ ተመሳሳይ ‹‹ክብር›› አላቸው ተብለው ወደሚታመኑ ‹‹ቅዱሳት›› ቦታዎች እንደ ማዳ ዋላቡ፣ ሆራ፣ አርሳዲ ያሉ የተከበሩ ቦታዎችም በቅዱሳት መካናትና ሊጠቀሱ ይችላሉ *Ardaa-Jilaa* /አርዳ ጅላ/ ወይም ልዩ ‹‹መንፈሳዊ›› ጉዞ ይደረግባቸዋል፡፡[68]

---

[65] ታሲላ እና ማርሳን፣ ገጽ 10::

[66] Dirribii, pp. 29-30.

[67] በኃሮ፣ ገጽ 31 ፡፡

68 Dirribii, p. 33 ፤ አቶ ቤኛ (ቃለ መጠይቅ)፡፡

### ፬.፬ ሥርዐተ ጋብቻ

ለጋብቻ የማይመረጡ ቀናት ፡- የኦሮሞ ብሔረሰብ ለጋብቻ ተስማሚ (ሙሉ) የሆኑትን ቀናት የሚያስወስነው "beekaa" (‹‹አዋቂዎችን››) ጠይቆ ነው፡፡ እንደነርሱ እምነት ጎደሎ ቀናት አሉ፤ ‹‹cagginoo›› (ጫጊኖ) ይሏቸዋል፡፡ በአብዛኛው ኦሮሞ ዘንድ ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ ብቻ ለጋብቻ የሚመረጡ ቀናት ናቸው፡፡ በተለይ ቅዳሜና ማክሰኞ የቦራና ስብሰባ (የኦሮሞ በኩራት ጉባኤ) ቀናትም ስለሆኑ፣ የቦራንቲቻ በዓል የሚከበርባቸው ቀናትም ናቸው፡፡ ሰኞ የኤኬራ ቀን ነው ሲሉ ረቡዕና ዓርብን ደግሞ የጾም ቀናት ስለሆኑ ለድግስ አይመቹም ባይ ናቸው፡፡[69] የጽሑፉ አቅራቢ ስለ እሑድ አለመመረጥ ግን በቂ አመክንዮ አላገኘም፡፡

**ዝምድና የመንጻት ሥርዐት በጋብቻ** ፡- በኦሮሞዎች ዘንድ የዘመዳሞች ጋብቻ ፈጽሞ የተወገዘ ነው፤ በእስልምናው ተጽእኖ ሥር የሚገኙት አንዳንዶች የአጎት/የአክስት ልጅ ጋር ቢጋቡም፣ ከጥንቱ ግን ልክ እንደ ፍትሐ ነገሥቱ ሁሉ እስከ ሰባት ትውልድ የሚደነግግ ሥርዐት ነበራቸው፡፡

ለልጆቻቸው የትዳር አጋር በሚያፈላልጉበት ጊዜም ይኸው ሥጋዊ ትስስር እንዳይኖር ማረጋገጥ ቀዳሚው ተግባራቸው ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ በስሕተት እንኳ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ቢጋቡ ወይም ሳይጋቡ ተራክቦ ቢፈጽሙ haraamuu (ሐራሙ) ይሰኛሉ፤ ‹‹ነውረኛ›› እንደማለት ነው፡፡ ብሔሩ ሥነ ምግባር ደንብ መሠረትም በአያንቱ (የሃይማኖት መሪ) አማካይነት ልዩ የመንጻት ሥርዐት ይፈጸምላቸዋል፡፡ አፈጻጸሙ እንዲህ ተጽፏል፡-[70]

> *‹‹ወደ ሆራ (ጠበል ቦታ) ይወስዷቸውና* dhiigatu dhiigatti makame, ya Waaq nu qulleessi *(ደም ከደም ተቀላቅሏልና አቤቱ አንተ አንጻን) ብለው ወደ ዋቃ (እግዚአብሔር) ይጸልያሉ፤ ጠጉራቸውን ላጭተው ይቀብሩታል፤ ሰውነታቸውን በልዩ (ቀለዋ) ቅጠል ካሹ በኋላ በሆራ (ጠበል) ይለቀልቋቸዋል፤ ምንጣፋቸውንና ደጃፋቸውንም እንዲሁ በሆራ ውኃ ይወለውላሉ፤ አዲስ ልብስ ያለብሷቸዋል፡፡››*

**የማጠቃለያ ሃሳብ**

በአሁኑ ጊዜ የተለየ መልክ ይዘው የሚገኙ የብሔረሰቡ አንዳንድ ድርጊቶች በባዕድ አምልኮነታቸው ተፈርጀው እንጂ፤ በተለየ ዓይን ታይተው እንደማያውቁ የዚህ ጥናት መነሻ ግምት ነበር፡፡ ከግምትም ባለፈ በጥናቱ ሂደት ከታዩ ሁኔታዎች ተመሳሳይ አዝማሚያዎችን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን የኦሮሞ ባህላዊም ሆነ ሥርዐተ አምልኮአዊ ክንውኖች ሙሉ በሙሉ ‹‹ባዕድ አምልኮ›› እንዳልሆኑ ይህ ጥናት አመላክቷል፡፡ ስለዚህም እነዚህ የብሔሩ ድርጊቶችና እምነቶች በአግባቡ ተጠንተውና ከክርስትናው አስተምህሮ ጋር ተገናዝበው ቢቀርቡ (ተገናዛቢነታቸውን እንደ ምቹ አጋጣሚ መጠቀም ቢቻል) ደግሞ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የወደፊት እንቅስቃሴ መልካም መሠረት ለመጣል፣ ሐዋርያዊ ተልእኮዋንም ለማፋጠን እንደሚያግዝ አያጠራጥርም፡፡ በመሆኑም ይህንን ውጤት እንደየአስፈላጊነቱ በየመዋቅሩ ያሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች በበጎ ገጽታ እንዲጠቀሙበት እንጂ፤ ያለ በቂ መረጃ ሙሉ በሙሉ ‹‹ባዕድ አምልኮ ናቸው›› ብሎ ማውገዙ የርትዕት ሃይማኖት ርቱዕ አካሔድ አይደለም፡፡

---

[69] ታሲላ እና ማርሳን፣ ገጽ 10::

[70] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 25

ምንም እንኳ እስካሁን በነበረው ሂደት እነዚህን የኦሮሞ ብሔር ባሕላዊ /ሥርዐተ አምልኮው ድርጊቶች ከቤተ ክርስቲያኒቱ እምነትና ሥርዐት ጋር የማዛመድ ጥረት መኖሩን የዚህ ጥናት አቅራቢ ባያውቅም፣ እንዲህ ሊያመሳስላቸው የቻለ ‹‹አንድ የታሪክ አጋጣሚ›› እንደሚኖር ግን ይገምታል፡፡ ይህ ጥናት ግን ይህንን እውነታ ከሚያፈላልጉት አካላት ‹‹አንዱ›› እንጂ፤ ‹‹ብቸኛ›› ሊሆን አይደፍርምና ለመሰል ምርምሮች ፍንጭ ለመስጠት ያህል በዚህ መልክ ቀርቧል፡፡

በዋናነትም ይህ ተመሳሳይነት መቼና እንዴት ሊከሰት ቻለ? የሚለው ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ በምልዐት ያልተዳሰሰና ወደፊት በስፋት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ቢሆንም ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከዐፄ ልብነ ድንግል በፊት ስለነበረው የኢትዮጵያ ታሪክ ሲጽፉ፡-

> *‹‹በኢትዮጵያ መጀመርያ የካም/የኩሽ ዘር ይኖር ነበር፤ በኋላ የሴም ዘር (ነገደ ዮቅጣን/አግዓዝያን) መጥቶ አሸነፈውና ተቀላቀለው፡፡… በኋላም ከነገደ እስራኤል፣ ከዐረብ፣ ከሕንድ፣ ከፋርስ፣ ከግሪክ ጋር በመደባለቁ ይህንን ድብልቅነቱን ለመግለጽ ዐረቦች ‹‹ሐበሽ›› አሉት፡፡››*

ያሉት ለቀጣይ ምርምር እንደ ፍንጭ ሊሆነን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ይህ ‹‹ድብልቅነት›› የዝርያ መወራረስ ብቻ ሳይሆን፤ ኢ-ቁሳዊ (intangible) የሆኑ ባሕላዊና ሥርዐተ ሃይማኖታዊ ድርጊቶችንም ወደ መዋዋስ ሊያሸጋግር እንዲቻለ አያጠያይቅምና፡፡